አዲስ ዘመን
እፎይ
እሁድ 82ኛ ዓመት ቁጥር 169 የካቲት 19 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# በኦሮሚያ በድርቅ አደጋ ለተጋለጡ

## ከ3 ነጥብ 6 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ድጋፍ እየተደረገ ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፦ በኦሮሚያ ክልል በድርቅ አደጋ ለተጋለጡ ከ3 ነጥብ6 ሚሊዮን በላይ ዜጎች የምግብ ድጋፍ እየተደረገላቸው መሆኑን ቡሳ ጎኖፋ ኦሮሚያ አስታወቀ።

የቡሳ ጎኖፋ ኦሮሚያ ሰብሳቢ ኮሚሽነር ሙስጠፋ ከድር በክልሉ በተከሰተው ድርቅ ዙሪያ በትላንትናው ዕለት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳሉት፤ የድርቁ ሁኔታ እየተባባሰ በመምጣቱ ቀደም ብሎ በ8 ዞኖች 3 ነጥብ 2 ሚሊዮን የነበረው የእርዳታ ፈላጊ ዜጎች ቁጥር በአሁኑ ወቅት በ10 ዞኖች ወደ 3 ነጥብ 6 ሚሊዮን ከፍ ብሏል። በአሁኑ ጊዜም 3 ነጥብ6 ሚሊዮን በላይ ዜጎች በድርቅ ምክንያት የምግብ ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛል።

በድርቅ ለተጎዱ 3 ነጥብ 6 ሚሊዮን በላይ ዜጎች 2 ነጥብ 1 ሚሊዮን በላይ ኩንታል የተለያዩ የእህል አይነቶችን እስከ ባለፈው ሳምንት ድረስ ተደራሽ ማድረግ ተችሏል ያሉት ኮሚሽነር ሙስጠፋ ፤ በዚህም ከ8 ቢሊዮን በላይ የሚገመት ገንዘብ ለድጋፍ ወጪ መደረጉን አስረድተዋል።

መኪና በማይገባባቸው እና የድጋፍ የምግብ እህል ባልደረሳቸው የክልሉ አካባቢዎችም በመንግሥት፣መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችን በማስተባበር አንድ ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር በላይ በጥሬ ገንዘብ ተደራሽ በማድረግ እህል ገዝተው እንዲጠቀሙ ማድረግ መቻሉን ኮሚሽነሩ ጠቅሰዋል።

አቶ ሙስጠፋ እንዳሉት፤ በክልሉ ለድርቅ ተጋላጭ



ፎቶ፦ ሔኖክ አብርሃ

ኮሚሽነር ሙስጠፋ ከድር

በሆኑ በአስሩም ዞኖች 102 የውሃ ቦቴዎች ለሰውና ለእንስሳት ውሃ እያቀረቡ ሲሆን ለእንስሳት መኖ የሚውል ከ186 ሺህ በላይ እስር ሣርም ቀርቧል።


በኦሮሚያ በድርቅ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




አቶ ታሪኩ ረታ



አቶ ጀግኑ ሙስታ



ወ/ሮ ሸጉ ተሰማ

# “የነዋሪነት መታወቂያ እድሳት እንዲደረግልን ከጠየቅን አንድ ወር ቢሆነንም ማግኘት አልቻልንም”

- ነዋሪዎች

# “ችግሩ ዘላቂ መፍትሔ እንዲያገኝ ኤጀንሲው ከከተማ አስተዳደሩ ጋር እየሠራ ነው”

- የአዲስ አበባ ወሳኝ ኩነት

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፦ የነዋሪ መታወቂያ እድሳት ለማድረግ ከጠየቅን አንድ ወር አልፎናል፤ የሚመለከተው አካል ችግሩን በፍጥነት ሊፈታልን ይገባል ሲሉ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች አሳሰቡ። የአዲስ አበባ ወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ በበኩሉ፤ ችግሩ ዘላቂ መፍትሔ እንዲያገኝ ኤጀንሲው ከከተማ አስተዳደሩ ጋር እየሠራሁ ነው ብሏል።

የልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሰባት ነዋሪ አቶ ቸርነት ድንቁ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በልደታ ክፍለ ከተማ የነዋሪ መታወቂያ ለመውሰድ ከተመዘገብኩ አንድ ወር አልፎኛል። መታወቂያ እንዳልተሠራልኝ


“የነዋሪ መታወቂያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


የሴቶችና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
Ministry of Women and Social Affairs

# በግማሽ ዓመቱ

## ከስደት የተመለሱ 97 ሺህ 303 ዜጎች ወደ ቀያቸው ተሸኝተዋል

**ማሕሴት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፦ ባለፉት ስድስት ወራት ከስደት የተመለሱ 97 ሺህ 303 ዜጎች አስፈላጊው የገንዘብና የሥነ ልቦና ድጋፍ ተደርጎላቸው ወደ ቀያቸው መሸኘታቸውን የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር ገለጸ።



በግማሽ ዓመቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል













**የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ተግባራዊ መሆን አፍሪካዊ ወንድማማችነትን ይበልጥ ያጠናክራል**


ገጽ 4






ፎቶ፡- ዳኜ አበራ

## “የዓድዋ ድል የኢትዮጵያ ብሔራዊ የክብር ማሕተምና የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ቀንዲል ነው”

- ብርጋዴር ጄኔራል ጌታቸው ዓሊ

**ውብሸት ሰንደቁ**

ሆለታ፡- የዓድዋ ድል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ክብር ማሕተም እና የመላው ጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ቀንዲል ነው ሲሉ የኢትዮጵያ ወታደራዊ አካዳሚ ዋና አዛዥ ብርጋዴር ጀኔራል ጌታቸው ዓሊ ገለጹ። ሆለታ ገነት በሚገኘው የኢትዮጵያ ወታደራዊ አካዳሚ 127ኛውን የዓድዋ ድል በዓል የሚዘክር ዝግጅት ትናንትና ተካሂዷል፡፡

በዝግጅቱ ላይ ብርጋዴር ጀኔራል ጌታቸው ባደረጉት ንግግር፤ የዓድዋ ድል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ክብር ማሕተም እና የመላው ጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ቀንዲል እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

የዓድዋ ድል ሊገኝ የቻለው ጀግኖች አያቶቻችን በከፈሉት ከፍተኛ መስዋዕትነት እና ባደረጉት ቆራጥ ተጋድሎ በመሆኑ ምንጊዜም ሊዘከር ይገባልም ሲሉ አክለው ተናግረዋል።

ጀግኖች አያቶቻችን በዓድዋ ላይ ያገኙት ድል ጥቁር ሕዝቦች በነጮች ወታደራዊ ኃይል ላይ ያስመዘገቡት ታሪካዊ ድል እንደሆነ ገልጸውም፤ ድሉ የተስፋፊዎችንና የወራሪዎችን ሕልም ያመከነ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች የድል ቀን፤ ለመላው ጥቁር ሕዝቦች ደግሞ የነፃነት ቀንን ማጎናጸፍ የቻለ ታላቅ ድል ነው ብለዋል።

የዓድዋ የድል በዓል ዛሬ ላለነው ትውልድ አንገታችንን ቀና አድርገን በነፃነት እንድንራመድ ያደረገን ዓለምን ያስደመመ እና የነጭ የበላይነትን ያኮሰሰ ታላቅ ድል በመሆን ሲታወስ የሚኖር ነው ያሉት ብርጋዴር ጀኔራል ጌታቸው፤ የዚህ በዓል መከበር ኢትዮጵያ ታፍራና ተከብራ እና አንድነቷና ነፃነቷ ጠብቃ የኖረች ሀገር መሆኗን ለመዘከር ብቻ እንዳልሆነ ጠቁመዋል፡፡

ይልቁንም ቀደምት አያቶቻችን ለሀገር አንድነት የከፈሉትን ታላቅ ዋጋ በማሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ሐይማኖት ሳይለያየን የተረከብናትን ታሪካዊት ሀገር ፀንተን በመጠበቅ ታሪካዊ ኃላፊነታችንን በመወጣት ለሚቀጥለው ትውልድ ጭምር ለማስተላለፍ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በመስዋዕትነት የተገኘውን የዓድዋን ድል በዓል ስናከብር የቀደምት አባቶችን የአይበገሬነት ወኔ በመላበስ መሆኑን የተናገሩት አዛዡ፤ታሪክ ተረካቢ መሆናችንን በመገንዘብ በተሠማራንበት የሥራ ዘርፍ ሁሉ ሀገራችንን በቅንነት በማገልገል በቁርጠኝነትና በታማኝነት የተጣለብንን ኃላፊነት እንድንወጣ በታላቅ አደራ ጭምር ለማሳሰብ እወዳለሁም ብለዋል።

# የጤና ተቋማት የግዥ ፍላጎታቸውን በወቅቱ አለማሳወቃቸው የመድኃኒት አቅርቦትና ፍላጎት እንዳይጣጣም አድርጓል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- የጤና ተቋማት ግዥ እንዲፈጸምላቸው የሚያስፈልጋቸውን የመድኃኒት ዓይነትና መጠን ለይተው በወቅቱ አለማቅረባቸው የመድኃኒት አቅርቦትና ፍላጎት እንዳይመጣጠን አድርጓል ሲል የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት ገለጸ፡፡ ለሚቀጥለው ዓመት ለመድኃኒት ግዥ 16 ቢሊዮን ብር እንደሚያስፈልገውም ገልጿል፡፡

በኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት የትንበያ ዳይሬክተር ተወካይ አቶ አባይነህ ላንዱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ የመድኃኒት ፍላጎትና አቅርቦት አለመመጣጠን ይታያል፡፡ የዚህ መንስኤው ደግሞ የጤና ተቋማት ግዥ እንዲፈጸምላቸው የሚፈልጉት የመድኃኒት ዓይነትና መጠን ለይተው በወቅቱ ለኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት ባለማቅረባቸው ነው፡፡ በዚህም በሀገሪቱ የመድኃኒት እጥረትና አንዳንድ መድኃኒቶች ከሚፈለገው መጠን በላይ ሲቀርቡ ቆይቷል ፡፡

አገልግሎቱ በጤና ተቋማት የሚስተዋለውን የመድኃኒት አቅርቦትና የሕክምና መሣሪያዎች ተግዳሮቶች ለመፍታት እየሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል። የመድኃኒትና የሕክምና መሣሪያዎችን አቅርቦትና ፍላጎትን ማመጣጠን እንደሚገባው ገልጸው፤ አገልግሎቱ የግዥ ሥርዓት ለማዘመን፣ የመድኃኒትና ሕክምና መሣሪያዎች አቅርቦት ለማሻሻል፣ ብልሹ አሠራሮችን ለማስተካከል ትኩረት ተደርጎ እየሠራ ነው ብለዋል።

አገልግሎቱ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ አቅርቦት የመድኃኒትና የሕክምና መሣሪያዎችን ችግርን እንደሚፈታ አቅጣጫ አስቀምጦ በተያዘው ዓመት የ2016 ዓ.ም የመድኃኒት ፍላጎት ለማወቅ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ባሉ 19 የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት ቅርንጫፎች በኩል ሁሉም የጤና ተቋማት የሚፈልጉትን የመድኃኒት መጠንና ዓይነት ለይተው እንዲያቀርቡ መደረጉን አቶ አባይነህ ተናግረዋል፡፡

በዚህም በ2016 ዓ.ም አገልግሎቱ ለመድኃኒት ግዥ 16 ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር እንደሚያስፈልግ ማረጋገጡን ተናግረዋል፡፡

ከዚህ በፊት የመድኃኒት እጥረት ሲኖር ተጠያቂው አንድ አካል ብቻ ይሆን ነበር ያሉት አቶ አባይነህ፤ለመድኃኒትና የሕክምና መሣሪያዎች የፍላጎት ከጤና ተቋማት በትክክል ተለይቶ እንዲመጣ መደረጉ ሁሉም አካል ኃላፊነት እንዲሰማው እንደሚያደርግም አመልክተዋል፡፡

አቶ አባይነህ የመድኃኒት አቅርቦት አገልግሎት ብቸኛው የመንግሥት መድኃኒት አቅራቢ ድርጅት መሆኑ በየጊዜው ለሚያጋጥመው የመድኃኒት አቅርቦት እጥረት አንዱ ምክንያት ነው ብለዋል ፡፡

የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅርቦት አገልግሎት የሀገሪቱን ከ90 በመቶ በላይ የመድኃኒት ፍላጎትን እንደሚሸፍን ገልጸው፤በቀጣይም በአቅርቦቱ ላይ ትልቁ ማነቆ የሆነው የሀገር ውስጥ አቅራቢዎች መዳከም እና በጤና ተቋማት ላይ ያለው የአቅርቦትና የፍላጎት ያለመጣጣም ችግሮች ለመፍታት የሚሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት በኢትዮጵያ የሕይወት አድንና መሠረታዊ መድኃኒቶችን እንዲሁም የሕክምና መሣሪያዎችን ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገራት እየገዛ ለማኅበረሰቡ እያቀረበ ያለ ተቋም ነው፡፡

# በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ በኢኮኖሚው ዘርፍ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት እየተሠራ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት “በኢትዮጵያ ታምርት” ንቅናቄ ከግብርናው ወደ ኢንዱስትሪ ለመሸጋገር በኢኮኖሚው ዘርፍ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት እየሠራ መሆኑን የኢንዱስትሪ ሚኒስትር አቶ መላኩ አለበል ገለጹ። በዘንድሮው ዓመት የአምራች ኢንዱስትሪው እድገት ወደ 10 ነጥብ 6 በመቶ ለማሳደግ መታቀዱን ጠቁመዋል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር አቶ መላኩ አለበል የፌዴራል እና የክልል የሥራ ኃላፊዎች በተገኙበት ”የኢትዮጵያ ታምርት” ንቅናቄ መድረክ ትናንት በባህር ዳር ከተማ ሲካሄድ በኢትዮጵያ በአምራች ኢንዱስትሪው ላይ የተመሠረተ ዕድገትና ብልጽግና ለማረጋገጥ በትኩረት እየተሠራ ነው ብለዋል።

በዚህም ”የኢትዮጵያ ታምርት” ንቅናቄ በመምራት በሁሉም ክልሎች ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የተሠራው ሥራ በብዙ ችግሮች አልፎ ለውጥ እያመጣ መሆኑን ገልጸዋል።

ባለፈው ዓመት 4 ነጥብ 6 በመቶ የነበረውን የአምራች ኢንዱስትሪ እድገት ዘንድሮ ወደ 10 ነጥብ 6 በመቶ ለማሳደግ መታቀዱን ጠቁመው፤በአምራች ኢንዱስትሪው የሚፈጠረው የሥራ እድል የተፈጠረላቸው ዜጎች ከ340 ሺህ በላይ ማለፉን ነው ሚኒስትሩ ያስረዱት።

የአማራ ክልል ለኢንቨስትመንት በሰጠው ትኩረት በአምራች ኢንዱስትሪው አበረታች ለውጥ አምጥቷል ያሉት ሚኒስትሩ፤ የአገር ውስጥ እና የውጭ ባለሃብቶች ማምረት የሕልውና መሠረት መሆኑን በመገንዘብ የጀመሩትን የኢንቨስትመንት ሥራ አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጥሪ አቅርበዋል።

መንግሥት በኢንቨስትመንት ዘርፉ የነበሩ ማነቆዎችን ደረጃ በደረጃ የመፍታት እንቅስቃሴ አጠናክሮ እንደሚቀጥልም አመልክተዋል።

የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ በበኩላቸው በአምራች ዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት ክልሉ በየደረጃው የኢንቨስትመንት ቦርድ አቋቁሞ ወደ ሥራ መግባቱን ገልጸዋል።

እንደ ኢዜአ ዘገባ የቦርዱ ዋና ግብ ባለሃብቶች የሚያቀርቡትን የቦታ እና ሌሎች ጥያቄዎችን በአፋጣኝ መፍታት የሚያስችል መሆኑን አመልክተዋል።

ክልሉ የማዕድን፣ የቱሪዝም፣ ግብርና፣ አግሮ ፕሮሰሲንግና ሌሎች የኢንቨስትመንት ዘርፎች እምቅ ፀጋ ያለው ነው ብለዋል።

የሀገር ውስጥ እና የውጭ ባለሃብቶች በክልሉ የተመቻቸውን የኢንቨስትመንት ሁኔታ በመጠቀም መዋዕለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱ ርዕሰ መስተዳድሩ ጥሪ አቅርበዋል።



አቶ መላኩ አለበል

ከንቅናቄ መድረኩ ጎን ለጎን የኢንዱስትሪና የግብርና ምርቶችን የሚያሳይ የኤግዚቢሽንና ባዛር ተከፍቷል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሕዝቡ የለውጥ አቅም ሆኖ የሚዘልቅበትን የመረጃ ሥርዓት ለመፍጠር!

መረጃና ከመረጃ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ለአንድ ማኅበረሰብ ያላቸው ጠቀሜታ የሕልውና ያህል ሊሆን እንደሚችል ይገመታል ፤ ከዚህ የተነሳም ባለንበት የመረጃ ዘመን ቀርቶ ቀደም ባሉት ዘመናት ዓለም ለመረጃ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥታ ለመንቀሳቀስ የተገደደችበት እውነታዎች ከፍተኛ ነበሩ።

ለዚህም በተለያዩ የዓለም ክፍል ያሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች ዘመናት ያስቆጠሩ የመረጃ ማስተላለፊያ ሥርዓት ባለቤት መሆናቸው፤ ዛሬም ቢሆን በእነዚህ የመረጃ ማስተላለፊያ ሥርዓታቸው በመታገዝ ሕይወታቸውን እየገፉ መገኘታቸው ለእውነታው ተጨባጭነት ማሳያ ተደርጎ ይወሰዳል።

ከሰው ልጆች የዕለት ተዕለት ሕይወት ጋር ተነጥሎ የማይታየው የመረጃ ጉዳይ ፤ ባለንበት ዘመን/በመረጃ ዘመን/ለሰው ልጆች ነገዎች አልፋና ኦሜጋ መሆን ወደሚያስችለው ታሪካዊ ምዕራፍ ለመሸጋገር በመንደርደር ላይ እንዳለ በስፋት ይነገራል፤ በርግጥም እየሆነ ያለው ከዚህ የተለየ አይደለም።

በተለይም ዓለም ወደ አንድ መንደርነት እየተለወጠች ባለችበት አሁናዊ ዓለም አቀፋዊ ዐውድ፤የመረጃ ማሰራጫ ቴክኖሎጂዎች ላይ እየታየ ያለው ፈጣን እድገት፤ እድገቱ በሰዎች የአኗኗር ዘይቤ ላይ እያሳደረ ያለው ተጽዕኖ እውነታውን አምኖ ለመቀበል በራሱ በቂ ነው።

የመረጃ ማሰራጫ ቴክኖሎጂዎች በከፍተኛ ሁኔታ እየዘመኑ ባሉበት ፤ ከዚህ የተነሳም ግለሰቦችን በያዟቸው ተንቀሳቃሽ ስልኮች በቀላሉ ዓለም አቀፍ የመረጃ ማሰራጫ የቴክኖሎጂ ሥርዓት ውስጥ የመግባታቸው እውነታ ትክክለኛ ሚዛናዊ መረጃዎችን ለሕዝብ የማሰራጨቱን ሂደት ፈታኝ አድርጎታል።

ይህ ዓለም አቀፋዊ እውነታ ቀደም ባለው ጊዜ መረጃ ሰብስቦ በማሰራጨት ወቅት የነበረውን ሂደት ተዓማኒ ለማድረግ በሙያ ሥነ ምግባርና በሕግ አግባብ ለመግራት ይደረግ የነበረውን ጥረት ፈተና ውስጥ ጨምሮታል። በዚህም ዓለም ያልተገባ ዋጋ ለመክፈል እየተገደደች ነው።

ትክክለኛ ፣ግልጽ እና ሚዛናዊ መረጃ ለሕዝብ እንዲሰራጭ ፤መረጃ የማሰብሰብና በማሰራጨት ሥራ ባለቤት የሆነው የጋዜጠኝነት ሙያ ሳይቀር ለተቀመጡለት ሙያዊ ሥነ ምግባሮችና የሕግ አግባቦች ለመገዛት እየተቸገረ ለአደጋ ተጋላጭ እየሆነ ነው።

ችግሮቹ በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ጡቦች በአግባቡ ባልተሰደሩባቸው ሀገራት ፤ ሥርዓቱን ለመገንባት ለሚደረጉ ጥረቶች ተግዳሮት ሆነው መታየት ከጀመሩ ውለው አድረዋል። እያስከተሉት ያለውም አደጋ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታውን ወደኋላ እስከ መጎተት የደረሰ ነው።

አንድም ሕዝቡ ይዞት ከመጣው የመረጃ አጥርቶ የማድመጥና የመውሰድ ክፍተት ጋር በተያዘ ፤በሚሰማው ሁሉ የመወሰድ አደጋ ውስጥ መውደቁ ፤ ከዚያም በላይ ሕዝቡን በተሳሳቱ መረጃዎች ግራ በማጋባት የለውጡ አቅም እንዳይሆን የሚደረጉ እኩይ ተግባሮች ሕዝቡ በቴክኖሎጂዎቹ በተገቢው መንገድ ተጠቃሚ እንዳይሆን እያደረጉት ነው።

የፖለቲካ ባሕላችን ሀሳብ ከመሞገት ይልቅ ስድድብና ብሽሽቅ ላይ የሚንጠላጠል ፤ለዚህም ማኅበራዊ ሚዲያውን ጨምሮ አዳዲስ ዘመናዊ የመረጃ ማሰራጫ ቴክኖሎጂዎችን ሳይቀር ኃላፊነት በጎደለው መንገድ የሚጠቀም፤ይህንንም አንድ የፖለቲካ ስትራቴጂ አድርጎ የሚወስድ መሆኑ የአደጋው አንዱ መገለጫ ሆኗል።

አንዳንድ የማኅበረሰብ አንቂ ነኝ የሚሉ አካላትም ቢሆን ራሱ በአግባቡ ሳይነቃ ሌሎችን ለማንቃት እየሄደበት ያለው መንገድ "በአይነስውር በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ " እንደሚባለው ሕዝባችን ትክክለኛ ፣ ግልጽ እና ሚዛናዊ መረጃ የማግኘት መብቱን ከማሳጣት ባለፈ በተሳሳተ መረጃ የእራሱን እና የሀገሩን ነገዎቹን ለአደጋ እንዲያጋልጥ እያስገደዱት ነው።

ይህንን ሃገራዊ ችግር ተሻግሮ ለማለፍ ከሁሉም በላይ ሕዝባችን መረጃዎችን ወስዶ የራሱ ከማድረጉ በፊት መረጃውን የማጥራት ባሕል ማዳበር እንዲሁም ትዕግስትና ስክነት መፍጠር ይጠበቅበታል። በተለይም ከፖለቲከኞች እና ከማኅበረሰብ አንቂዎች ከሚለቀቁ መረጃዎች ጀርባ ያሉ ድብቅ ዓላማዎችን በአግባቡ መገንዘብ የሚያስችል እርጋታ ሊኖር ያስፈልጋል ።

በተለያዩ የመንግሥት መዋቅር ውስጥ የሚገኙ የመንግሥት ኃላፊዎችም ፤ኅብረተሰቡን ውዥንብር ውስጥ የሚጥሉ መረጃዎች ሲለቀቁ ፤ ፈጥነው ትክክለኛ መረጃዎቹን በማውጣት ሕዝቡ በተሳሳቱ መረጃዎች ያልተጋባ ዋጋ እንዳይከፍል መታደግ ይጠበቅባቸዋል። በዚህም ሕዝቡ የለውጡ አቅም ሆኖ የሚዘልቅበትን የመረጃ ሥርጭት ሥርዓት መፍጠር ይቻላል!

**አዲስ ዘመን**
ኢፕድ
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## መተማመንና ቅንነት ለሀገር መረጋጋትና ግንባታ

**ውዱ ፀሐይ**

ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ዘመናትን ተሻግራ የቆመችና ጠንካራ ሀገረ መንግሥት የገነባች ነች። ለዚህ ስኬት አስተዋፅዖ ያበረከቱት የጋራ እሴቶች፣ የደመቁ ታሪኮች፣ ዘመናትን የተሻገሩ ሀገር በቀል ዕውቀቶችና ዕውቀቶቹ ያፈሯቸው ሊቃውንቶች ባቆዩልን ጥበብ ነው። ከሁሉም በላይ ከሺህ ዘመናት በላይ ያስተሳሰራት፤ እህል የሞላውን ጆንያ እንደሚቋጥር ገመድ ዘመንን ከዘመን አሰናስሎ ያሻገራት ዋናው ሰንሰለት በሕዝቦቿ መካከል ያለው መተማመንና ቅንነት ነው።

ሀገር ጠንካራ ምጣኔ ሃብት ስላላት ብቻ አትፀናም። የተከለለ ድንበር፣ ተዝቆ የማያልቅ የተፈጥሮ ሃብት ባለቤት ስለሆነችም አትቀጥል። ሀገር በእድገትና በአንድነት ወደ ፍፁማዊነት በተጠጋ አብሮነት ወደፊት እንድትራመድ በአንድ ጣሪያ ስር የሚኖሩ ማኅበረሰቦች እርስ በእርስ ከፍፁም ቅንነት የመነጨ መተማመን ሊኖራቸው ይገባል።

ከዘመን ወደ ዘመን ስንሸጋገር አብሮነታችንን፣ መተማመንና አንድነታችንን ፈተና ውስጥ የከተቱ እክሎች የነበሩበት ወቅት እንዳለ የታሪክ ድርሳኖቻችን ቢያስታውሱንም ሰፊውን ድርሻ የሚወስደው ክፍል ግን ታላቅና ባለታሪክ ሀገር መገንባታችንን አስረግጦ የሚነግረን ነው። ለዚህ ነው ካለፉት ስንጥቆቻችን እየተማርን የዛሬውን ክፍተት መድፈን የብልህ አካሄድ ነው የምንለው።

መተማመን ራዕይን ያፀናል። እርስ በእርስ የሚኖረን መተማመን ወደፊት እንድንራመድና በተስፋ እንድንሞላ የሚረዳን ታላቅ አቅም ነው። ለዚህ ነው በአብሮነታችን ግዜ፤ የጋራ በሆነችው ኢትዮጵያ ከሁሉም በላይ መግባባትና መተማመን ላይ መድረስ የሚኖርብን።

ባለፉት የፖለቲካ እጥፋቶቻችን ውስጥ ባለመደማመጣችንና ባለመተማመናችን ብዙ ጠባሳና ቁስሎችን አትርፈናል። በሕዝቦች መካከል ጥርጣሬን ያነገሱ፣ ፍቅርን ያቀዘቀዙና ጭካኔን ያሰፈኑ አያሌ ችግሮች ገጥመውናል። ከእነዚህ ስብራቶቻችን ትምህርት መውሰድ ይጠበቅብናል።

በአንደኛው የታሪክ ክፍላችን 60 እና 70 ዓመታትን ወደኋላ መለስ ብለን ስንቃኝ የንጉሡ ሥርዓት ላይ እምነት ያጡ ቡድኖች እንደነበሩ እናስታውሳለን። እነዚህ አዲስ አስተዳደር ለማፅናት ያቀዱ ግለሰቦች እና ሥርዓቱን ሲመራ የነበረው ንጉሣዊ ሥርዓት በመካከላቸው መተማመን ባለመፍጠራቸውና ቁጭ ብሎ ለመነጋገር የሚያስችል ባሕል ባለመኖሩ ምክንያት ሀገሪቱን ብዙ ዋጋ አስከፍሏታል ።

በተለምዶ የታኅሣሥ ግርግር እያልን የምንጠራው ክስተት ኢትዮጵያን ማገልገል የሚችሉና ወደፊት የማራመድ አቅም ያላቸው ግለሰቦችን ከመቅጠፉም ባሻገር መተማመናችን እና ለአንድ አገር በጋራ የመሥራት ባሕላችን ደካማ እንደነበር ማሳያ ሆኖ አልፏል።

በደርግ ዘመነ መንግሥት አዲሱ ሥርዓት መንበረ ሥልጣኑን ሲያፀና በቀድሞው የንጉሡ ሥርዓት ሲያገለግሉ የነበሩ በርካታ ምሑራን ወደ ሞት ተሸኝተዋል። ገሚሶቹም ወደ ከርቸሌ ገብተው እድሜያቸውን ጨርሰዋል። በዚህ ሀገር ዋጋ ከፍላለች። ከዚያ በላይ ግን በአንድነት ለምንኖርባት ሀገራችን በኅብረትና በፍፁም እምነት በውይይት ላይ ተመሥርተን አዲስ መንገድ ለመቀየስ እንደሚተናነቀን ይህ የታሪክ ክፍላችን አንድ ነገር ሹክ ይለናል።

ለምን ይሆን ታላላቅ የሚባሉ ለውጦችን በፍፁም አንድነትና ቅንነት ለሀገር ግንባታና ሽግግር ልንጠቀምባቸው ያልቻልነው? ለምንስ ነው ፍፁም መተማመንን ምግባራችን አድርገን ምቹ የፖለቲካ ባህል መገንባት ያቃተን? እነዚህን ጥያቄዎች አዲሱ ትውልድ መልስ ሊያገኝላቸው ይገባል።

ኢትዮጵያ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ በፈጣን የፖለቲካ ለውጥ ውስጥ ትገኛለች። ከ30 እና 40 ዓመት በፊት የነበረው ሥርዓት ዘመኑን ባለመዋጀቱ ለውጡን ጎትቶ ይዞት እንደመጣ ይታመናል። በዚህ ሂደት ታዲያ አሮጌው ሐዲድ ላይ የነበሩት በአቋማቸው በመፅናታቸው ምክንያት ወደ አዲሱ ለመግባት ከሚታገሉት ጋር ሰፊ ተቃርኖና ልዩነት እንዲፈጠር ሆኗል።

ባለፉት አራት ዓመታት ውስጥም በኢትዮጵያ ውስጥ አለመግባባት፣ ጦርነት፣ የሴራ ፖለቲካ በመከሰቱ ምክንያት በርካቶች ሞተዋል። ሕፃናት፣ ሴቶች አዛውንት እና በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው ለስደት ተዳርገዋል። በኢኮኖሚያችን ላይ ከባድ ስብራት ደርሶ ነበር። አሁንም ይህ ከድብታ ውስጥ አልወጣንም።

በሕዝቦች መካከል የነበረውን መተማመን የሚሸረሽሩ አያሌ እኩይ ተግባሮች ነበሩ። ከእዚህ መረዳት የምንችለው ቁጭ ብሎ ለመነጋገር፣ ለችግሮች መፍትሔ ለማምጣት ከመጣር ይልቅ አጥፊውንና ከባዱን መንገድ መምረጣችንን ነው። ይህን የጥፋት መንገድ እንድንከተል ያደረገን እርስ በእርስ የነበረን መተማመን በመሸርሸሩና በምትኩ መጠራጠር በመንገሡ ምክንያት ነው። ለዚህ ደግሞ ዋጋ ከፍለንበታል። ፖለቲካችን ታምሞ እንዲድህ ሆኗል።

ዛሬ አጥፊውን መንገድ መከተላችን ተገቢ አለመሆኑ የገባን ይመስላል። ችግሮችን ጠረጴዛ ዙሪያ ለማምጣት ወኔውን አግኝተናል። የጠፋ ሕይወት፣ ንብረትና የደረሰ የሰብዓዊ ጥሰት ከባድ ኪሳራ ውስጥ ከትቶን ቢሆንም ከዚህ እኩይ መንገድ ብዙ ሳንርቅ እና የበለጠ ጥፋት ሳይደርስ መመለሳችን እራሱ የሚያበረታታ ነው። ለዚህ ነው ፖለቲከኞቻችን፣ ማኅበረሰቡ፣ የማኅበረሰብ አንቂዎች፣ ተፅዕኖ ፈጣሪ ታዋቂ ሰዎች በመካከላቸው ፍፁም መተማመንና ቅንነት ሊኖራቸው ይገባል የምንለው።

ባለፉት ወራት በሰሜኑ ክፍል ተከስቶ የነበረውና ለሁለት ዓመታት የቆየው ጦርነት በጠረጴዛ ዙሪያ ለመፍታትና ለመቀራረብ እየተወሰደ የሚገኘው አበረታች እርምጃ ይበል የሚያሰኝ ነው። በውጪ ኃይሎች አጋዥነት ከኢትዮጵያ ውጪ የተደረገው ስምምነትም ወደ ሀገር ውስጥ ዘልቆ ተደጋጋሚ ውይይቶች፣ መተማመንን የሚያመጡ መቀራረቦች መፈጠራቸው ለሕዝቡ እፎይታን የሚሰጥ ትልቅ እርምጃ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል።

ከሁሉ በላይ ግን አዲስ የፖለቲካ ባህል የሚፈጥር በቀሪው የኢትዮጵያ ክፍል ለሚከሰቱ ደም አፋሳሽ ግጭቶች ተመሳሳይ መፍትሔ ለመፈለግ እድሉን የሚከፍት እንደሆነ ይሰማናል። ማንኛውም ግለሰብ ሃሳብ ካለውና ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ማገዝ ከፈለገ መንገዱ ሰላምና ሰላማዊ መሆን ይገባዋል።

ከሁሉ በላይ ከባላጋራውና ከተቀናቃኙ ጋር በጠረጴዛ ዙሪያ ለመቀመጥና ሀሳብ ለማፋጨት ጫንቃውን ሊያደነድን የግድ ይላል። ይህ ለዘመናት ኢትዮጵያን በፅኑ መሠረት ላይ ያኖራት የሕዝቦች አንድነት፣ መተማመንና ፍፁማዊ ቅንነት የፖለቲካ እጥፋት በገጠመን ቁጥር ስጋት ላይ እንዳይወድቅ ያግዘናል።

# የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ተግባራዊ መሆን አፍሪካዊ ወንድማማችነትን ይበልጥ ያጠናክራል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ተግባራዊ መሆን ለአፍሪካ እድገትና ብልጽግና ከማምጣት ባለፈ አፍሪካዊ ወንድማማችነትን እንደሚያጠናክር የናይጄሪያ ጋዜጠኛ ኪንግ ሪቻርድ ገለጹ።

የናይጄሪያ ጋዜጠኛ ኪንግ ሪቻርድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ እኛ አፍሪካውያንን አንድ የሚያደርገን የአንድ አህጉር ሕዝቦች መሆናችን ብቻ አይደለም። የምንጋፈጣቸውም ችግሮች ያመሳስሉናል። የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጠና መተግበሩም ለአፍሪካ እድገትና ብልጽግና ከማምጣት ባለፈ አፍሪካዊ ወንድማማችነትን ያጠናክራል።

36ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ መሪ ቃል "የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣናን" ጉዳይ ላይ በመሆኑ አፍሪካዊ አንድነት፣ እድገትና ብልጽግና እንዲሁም አፍሪካዊ ወንድማማችነትን እንዲኖር ያስችላል ያሉት ኪንግ ሪቻርድ፤ የንግድ ቀጣናው የአፍሪካ ድምፅ በዓለም መድረክ ጎልቶ እንዲወጣ ያደርጋል ብለዋል።

እንደ ኪንግ ሪቻርድ ገለፃ፤ አፍሪካዊ ወንድማማችነትን ለማጠናከር አፍሪካውያን በማኅበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ጉዳይ አንድ የሚያደርጋቸው ሥርዓት ሊኖር ይገባል። ለዚህም እንደ አፍሪካ ነጻ ገበያ አይነት እድሎች ትልቅ አስተዋፅዖ አላቸው።

የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና አፍሪካ በንግዱ ዘርፍ የተጋረጠባትን የተወዳዳሪነት ተግዳሮት ለመፍታት ዓይነተኛ መሣሪያ ነው። ከዚህም ባሻገር የኢኮኖሚ ውሕደትን ለማጠናከር እና የአፍሪካን ልማት ለማፋጠን የሚኖረው አንድምታ ትልቅ ነው። ይህም አፍሪካውያን በራሳቸው ቋንቋ እንዲግባቡ እና በአፍሪካውያን መካከል ቅርብ ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል ብለዋል።

የአፍሪካ ነፃ የገበያ ማዕከልን ለማቋቋም በሩዋንዳዋ ኪንሻሳ እኤአ በ2018 በተደረገው ስምምነት መሠረት ኢትዮጵያን ጨምሮ 40 አገራት እስካሁን ስምምነቱን በማፅደቅ ፊርመዋል ያሉት ኪንግ ሪቻርድ፤ ስምምነቱ በአፍሪካ የጋራ ሸቀጣ ሸቀጥ እና የአገልግሎት ዘርፍ እንዲኖር በማድረግ እና የኢኮኖሚ ቅንጅት በመፍጠር የአፍሪካን ኢኮኖሚ ለማሳደግ እንደሚጠቅም ተናግረዋል።

ይህ ሥራ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎችን ማድረግን ጭምር የሚጠይቅ በመሆኑ መሪዎች ለዚህ ዘርፍ እድገት የበኩላቸውን ድርሻ ሊወጡ ይገባል። በዚህ የጋራ ገበያ ላይ በተለይ ታሪፎችን መቀነስ እና በዘርፉ ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን መለየትና መፍታት ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ ሊሆን እንደሚገባም ጋዜጠኛው ምክረ ሀሳብ ሰጥተዋል።

እንደ ጋዜጠኛው ገለጻ፤ "ለአፍሪካዊ ችግር አፍሪካዊ መፍትሔ" የመፈለግ ጉዟችን ውስጥ ኢትዮጵያ በፕሪቶሪያው ስምምነት ያሳየችው ስኬት አህጉራዊ ስኬት እንደሚያመጣ አስባለሁ። ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት ለተያዙ ሀገራት የነፃነት ተምሳሌት ከመሆኗ ባለፈ የአፍሪካ እናት መሆኗ መረሳት የለበትም። ይህም የወዳጅነታችን መሠረቱ ጥቅም ሳይሆን እውነተኛ ወንድማማችነት መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

እኛ አፍሪካውያን የአንዳችን ቁስል ሌላችንን ማመሙ፤ የአንዳችን ሰቀቀን ለሌላችን መሰማቱ ጥብቅ ቤተሰቦች አድርጎናል ያሉት ኪንግ ሪቻርድ፤ በመንገዱ ላይ ዕንቅፋት ይገጥመን ይሆናል፤ ፈተናዎች ዕረፍት አልሰጥ ብለው እንቸገር ይሆናል፤ ነገር ግን እጅ ለእጅ ተያይዘን እናልፈዋለን በማለት ዛሬ የተሻገርነው ፈተና ለእኛ ትምህርት፣ ከእኛ በኋላ ለሚመጣው ትውልድ የጥንካሬ ምንጭ እንደሚሆን አልጠራጠርም ብለዋል።

# በኦሮሚያ በድርቅ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በቦረና ዞን ሁሉም ወረዳዎች ቆላማ በመሆናቸው ምክንያት 867 ሺህ በላይ ዜጎች በመንግሥትና በተለያዩ ተቋማት የምግብ እህል ድጋፍ እየተደረገላቸው እንደሚገኙ አመልክተው፤በዚህም ባለፉት ሰባት ወራት ወደ አንድ ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር የሚገመት 465 ሺህ በላይ ኩንታል የተለያዩ የእህል አይነቶች ለዜጎች ድጋፍ መደረጉን ገልጸዋል።

ኮሚሽነሩ መኪና በማይገባባቸው እህል ባልደረሰባቸው አካባቢዎች ላይ 623 ሚሊዮን ብር በላይ በጥሬው ገንዘብ ተደራሽ በማድረግ በአቅራቢያቸው ገዝተው እንዲጠቀሙ ለማድረግ መቻሉን ገልፀዋል። በዚህም ድጋፍ ላይ የፌዴራል እና የክልሉ መንግሥት ብሎም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማስተባበር ተደራሽ መደረጉን አብራርተዋል።

በአሁኑ ጊዜ በቦረና ዞን የውሃ እጥረት መኖሩን የገለጹት ኮሚሽነሩ፤ 27 ቦቴዎች በአስራ ሦስት ወረዳዎች ውሃን ተደራሽ በማድረግ ላይ ናቸው። በሌላ በኩል ለከብቶች መኖ የሚውሉ ከ139 ሺህ በላይ የታሰረ መኖ እስካለፈው ሳምንት ድረስ ተከፋፍሏል ብለዋል።

በሚቀጥለው ሁለት ወራት ዝናብ ሊኖር ስለማይችል የተጎጂዎችን ቁጥር ሊጨምር የሚችል በመሆኑ ድጋፉ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አስረድተዋል።

ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የክልሉ መንግሥት እየሠራ መሆኑን ገልጸው፤ በቆላማ ዞኖችና ወረዳዎች ላይ በውሃ ላይ የሚሠሩ ሥራዎች ተጠናክረው የቀጠሉ ሲሆን 72 ፕሮጀክቶችም ተቀርጸው የተጀመሩ መሆናቸውን ኮሚሽነሩ አመልክተዋል።

ኮሚሽነሩ ዝናብ ባለመዝነቡ እና ዝናብ በዘነበባቸው አካባቢዎች ላይም በቂ ዝናብ ባለመዝነቡ ምክንያት በደቡብ ምሥራቅ ኦሮሚያ ከቦረና እስከ ምሥራቅ ሐረርጌ ባሉ ዞኖች በ2014 ዓ.ም ስምንት ዞኖች ላይ ድርቅ መከሰቱን ገልጸው ፤3 ነጥብ2 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ሲረዱ መቆየታቸውን አስታውሰዋል።

# "የነዋሪነት መታወቂያ እድሳት እንዲደረግልን ከጠየቅን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ለመናገር ሄጄ ነበር። መታወቂያው ያልተሠራልኝ ምክንያት በክፍለ ከተማው ያለው መታወቂያ ማተሚያ ማሽን ስለተበላሸ መሆኑን ገልጸውልኛል። እስከ አሁንም መታወቂያ አላገኘሁም።

በዚህም የተነሳ የነዋሪነት መታወቂያ የሚፈልጉ አገልግሎቶችን ማግኘት እየቻልኩ አይደለም። ስለዚህ የሚመለከተው አካል የመታወቂያ አስፈላጊነትን በመረዳት ያለውን ችግር በፍጥነት እንዲፈታ አሳስባለሁ ብለዋል።

የልደታ ክፍለ ከተማ የወረዳ ሰባት ወሳኝ ኩነት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ጀግኑ ሙለታ በበኩሉ፤ በልደታ ክፍለ ከተማ ያለው ማሽን ተበላሽቶ ነበር። በዚህም ነዋሪዎች የመታወቂያ አገልግሎት ለማግኘት የተወሰነ ጊዜ ወስዶባቸዋል። ነገር ግን የመታወቂያ አስፈላጊነት ምን ያህል እንደሆነ ስለምናውቅ። ለችግሩ ጊዜያዊ መፍትሔ እና ነዋሪዎች ዲጂታል መታወቂያ እስኪሠራላቸው ድረስ የሚጠቀሙበት የመታወቂያ አገልግሎትን የሚተካ የወረቀት መታወቂያ ሰጥተናል።

ይህም የተደረገው ነዋሪዎች የወሳኝ ኩነት አገልግሎትን በመጡበት ሰዓት ማግኘት እንዲችሉ ነው ያሉት ኃላፊው፤ አሁን ግን ማሽኑ ስለተቀየረ አገልግሎቱ በፍጥነት እየተከናወነ እንደሆነ እና መታወቂያ ለመውሰድ የተመዘገቡ ሰዎች በፍጥነት እንደሚያገኙ ገልጸዋል።

ነገር ግን ነዋሪዎች በመጡበት ሰዓት የወሳኝ ኩነት አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ የመታወቂያ ማተሚያ ማሽን በወረዳ ጭምር ቢኖር ችግሩን በዘላቂ መንገድ መፍታት ይቻላል ብለዋል።

የልደታ ክፍለ ከተማ ወሳኝ ኩነት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ወይዘሮ ሸጉ ተሰማ እንደተናገሩት፤ በክፍለ ከተሞች መታወቂያ መታተም ከተጀመረ በኋላ አንድ ነዋሪ መታወቂያ ለመውሰድ በትንሹ አንድ ሳምንት ይፈጅበታል። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ልደታ ክፍለ ከተማ የሚጠቀመው አንድ የመታወቂያ ማተሚያ ማሽን ብቻ መሆኑ ነው።

ማሽኑ በቀን እስከ አምስት መቶ መታወቂያ ማተም ይችላል ያሉት ወይዘሮ ሸጉ፤ የመታወቂያ አገልግሎት ለማግኘት የሚመጣው አካል በቁጥር ከአምስት መቶ እንደሚበልጥ እና ነዋሪዎች መታወቂያን በአንድ ሳምንት እንዲያገኙ ለማድረግ የወሳኝ ኩነት ባለሙያዎች አምሽተው ከመሥራት ባለፈ የእረፍት ቀናቸውን ጭምር እየሠሩ እንደሆነ ገልጸዋል።

ይህም ማለት የመታወቂያ አገልግሎት ለማግኘት የሚመጣው አካል እና ክፍለ ከተማ ለአገልግሎት አሰጣጡ የሚጠቀመው ማሽን ተመጣጣኝ እንዳልሆነ ያሳያል ብለው፤ ማሽኑ አንድ ጊዜ አትሞ በጨረሰ ቁጥር ማረፍ እንዳለበት እና ማሽኑ ለትንሽ ቀናት አገልግሎት መስጠት እንዳልቻለ ተናግረዋል።

እንደ ወይዘሮ ሸጉ ገለፃ፤ የማሽኑ መበላሸት ነዋሪዎች መታወቂያ ለመውሰድ ከሳምንት በላይ እንዲጠብቁ አድርጓል። ነገር ግን ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅያሪ ማሽን አምጥተን መሥራት ከጀመርን ሁለት ሳምንት አልፎናል።

አሁን ላይ መታወቂያ ለመውሰድ እየጠበቁ ያሉ ሰዎች በፍጥነት መታወቂያ እንዲያገኙ እየሠራን ነው ያሉት ኃላፊዋ፤ ነዋሪዎች በመጡበት ሰዓት መታወቂያ እንዲያገኙ በክፍለ ከተማው ቢያንስ ሁለት እና ሶስት የመታወቂያ ማሽን እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

ኢፕድ በልደታ ክፍለ ከተማ ያለው ችግር በሌሎችም ክፍለ ከተሞች እየተፈጠረ መሆኑን ለማረጋገጥ ሌሎች ክፍለ ከተሞች ላይ ቅኝት አድርጓል። ከነዚህም ውስጥ አንዱ የአራዳ ክፍለ ከተማ ወሳኝ ኩነት ጽሕፈት ቤት ነው።

እንደ ጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ አቶ ታሪኩ ረታ ገለፃ፤ በአራዳ ክፍለ ከተማ የነዋሪዎች መታወቂያ በአምስት ቀን ውስጥ ማግኘት ይቻላል። ነገር ግን የመታወቂያ እግዱ ከተነሳ በኋላ በርካታ የሕዝብ ቁጥር ስናስተናግድ ስለነበር እና በአንዳንድ ችግሮች ምክንያት መታወቂያ ሳያገኙ ሁለት ወር የሚሞላቸው አካላት አይጠፉም።

ይህም ችግር አሁን ላይ እየፈታን እንገኛለን።

አራዳ ክፍለ ከተማ ለነዋሪዎቹ የመታወቂያ አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያደርገው በሁለት መታወቂያ ማተሚያ ማሽን እንደሆነም ኢፕድ ተገንዝቧል።

ሌላኛው የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ አቶ ሃብታሙ በለጠ (ስማቸው የተለወጠ) በበኩላቸው፤ የነዋሪ መታወቂያ ለመውሰድ ከአንድ ወር በላይ መጠበቅ የለብኝም። ምክንያቱም አንድ ዜጋ መታወቂያ ይዞ የመንቀሳቀስ ግዴታ አለበት። ከዚህም ባለፈ የነዋሪነት መታወቂያ የተለያዩ አገልግሎቶችን ለማግኘት ወሳኝ ነው። አገልግሎቶቹን ለማግኘት ደግሞ የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ ሊኖር ግድ ይላል።

ስለዚህ መታወቂያ የማደስ ስልጣን እና ኃላፊነት የተሰጠው አካል ኅብረተሰቡ የነዋሪነት መታወቂያን በሚፈልግበት ጊዜና ሰዓት የሚያገኝበት ሁኔታን ማመቻቸት አለበት ብለዋል።

ኢፕድ በተለያዩ ክፍለ ከተሞች ባደረገው ቅኝት ሁለት መታወቂያ ማተሚያ ማሽን ያላቸው ክፍለ ከተሞች እንዳሉ ሁሉ አንድ ማተሚያ ማሽን ያላቸው ክፍለ ከተሞች እንዳሉ ተረድቷል። በዚህም አንድ ማተሚያ ያላቸው ክፍለ ከተሞች የማሽን ብልሽት ሲያጋጥማቸው ነዋሪዎች መታወቂያ የሚያገኙበት ጊዜ እንደሚራዘምባቸው ተገንዝቧል።

ይህንን አስመልክቶ ኢፕድ ለሁሉም ክፍለ ከተሞች ሁለት ማተሚያ ማሽን ለምን አይሰጥም? ማተሚያ ማሽኑ በየወረዳውስ ለምን አይኖርም? ሲል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲን ጠይቋል።

የአዲስ አበባ ወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ በበኩሉ፤ ችግሩ ዘላቂ መፍትሔ እንዲያገኝ ኤጀንሲው ከከተማ አስተዳደሩ ጋር እየተነጋገረ ነው ብሏል።

የአዲስ አበባ ወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ የኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ዮሴፍ ንጉሴ እንደተናገሩት፤ የመታወቂያ ማተሚያ ማሽን በሁሉም ወረዳዎች እንዲኖር ማድረግ አይቻልም። ምክንያቱም ማሽኖቹ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚፈልጉ ናቸው። ይሁንና አንድ ማሽን ብቻ ላላቸው ክፍለ ከተሞች ግን ሁለት እንዲኖራቸው የማድረግ ሥራ እየሠራን ነው።

ማተሚያ ማሽኑ ውድ እና ከውጭ የሚመጣ በመሆኑ ለክፍለ ከተሞች ማሽኑን በፍጥነት መስጠት አይቻልም። ስለዚህ ተጨማሪ ማሽን እስኪመጣ የሚበላሹ ማሽኖች በፍጥነት እየተሠሩ ወደ ሥራ እንዲገቡ ይደረጋል ብለዋል።

ኤጀንሲው በአሁኑ ሰዓት ሁለት ተግዳሮቶች እያጋጠሙት ነው ያሉት አቶ ዮሴፍ፤ እነሱም አንደኛ የመሥሪያ ቦታ ችግር ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ የመታወቂያ ማተሚያ ማሽን ነው። ለዚህም ተግዳሮቶች የአጭር ጊዜ መፍትሔ ተዘርግቶላቸው ወደ ሥራ ገብተዋል። ከዚህም ውስጥ አንዱ የመታወቂያ አገልግሎትን የሚተካ የአክናሌጅመትን ፔፐር ተዘጋጅቶ ኅብረተሰቡ አገልግሎት እንዲያገኝ ተደርጓል። ነገር ግን ችግሮቹን ዘላቂ አድርጎ ለመፍታት ኤጀንሲው ከከተማ አስተዳደሩ ጋር እየተነጋገረ ነው ብለዋል።

# በግማሽ ዓመቱ ከስደት የተመለሱ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ሦስት ሚሊዮን 836 ሺህ 113 ሴቶች መብትና ጥቅሞቻቸውን ለማስከበር መደራጀታቸው ተመልክቷል።

የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ እንዳመለከተው፤ከስደት ተመላሽ ለሆኑ ዜጎች የሥነ-ልቦናና፣የማኅበራዊ አገልግሎቶችና ኢኮኖሚያዊ ድጋፎችን ለማድረግ ታቅዶ በግማሽ ዓመቱ 97 ሺህ 303 ዜጎችን ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ በመቀበልና አስፈላጊውን መረጃ በማደራጀት በማቆያ ማዕከላት አስፈላጊው ድጋፍ ተደርጎላቸዋል። 97 ሺህ 303 ዜጎችም አስፈላጊው የገንዘብና የሥነ ልቦና ድጋፍ ተደርጎላቸው ወደ ቀያቸው ተሸኝተዋል።

በማቆያ ማዕከላት አስፈላጊውን የሥነ-ልቦና እና ማኅበራዊ ድጋፍ የተሰጣቸው ከስደት ተመላሾች ፣ ጊዜያዊ የኑሮ መደጎሚያ ገንዘብና ቁሳቁስ ድጋፍ ተደርጎላቸው ወደ ቀያቸው ተመልሰው ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንዲቀላቀሉ መደረጉን በሪፖርቱ ጠቅሷል።

በተያያዘም ባለፉት ስድስት ወራት የሴቶች መብት፣ ተሳትፎና ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ሥራ ተሠርቷል ያለው መግለጫው፤ በተለይ የሴቶች ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማሳደግ ሁለት ሚሊዮን 799 ሺህ 045 ሴቶችን በማኅበራት ተደራጅተው በቁጠባ ተሳታፊ ሆነዋል። በዚህም የሚቆጥቡ ሴቶች ምጣኔ ወደ 30 በመቶ ማድረስ መቻሉን መግለጫው ያስረዳል።

ሴቶች በኅብረት ሥራ ማኅበራት በአባልነት እንዲሳተፉ በማድረግ የሴቶችን የብድር አገልግሎት ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ፤በገጠር የአገሪቱ ክፍል የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግም የካዳስተር የመሬት ባለቤትነት ማረጋገጫ እንዲያገኙ የማድረግ ሥራ እንደተሠራ ተገልጿል።

ከክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮችና ከፌዴራል ሴክተሮች ለተውጣጡ ሴቶች ዝቅተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ አመራሮች የአጭር ጊዜ የአቅም ግንባታ ሥልጠና በመስጠት ለአመራር ብቁ የሆኑ ሴቶችን የማፍራት ሥራ ተሠርቷል ብሏል መግለጫው፤ እንዲሁም 160 ሴቶችን በሃምሳ ሚሊዮን የአፍሪካ ሴቶች ይናገሩ ፕሮጀክት ተጠቃሚ ለማድረግ ባለሀብቶችን እና አጋር ድርጅቶችን በማስተባበር ድጋፍ እንዲያደርጉ ንቅናቄ መደረጉን ተገልጿል።

በአዳሪ ትምህርት ቤት ለሚገኙ ሴት ተማሪዎችም የትምህርት ቁሳቁስ፣ አልባሳትና የንጽሕና መጠበቂያ ድጋፍ መደረጉን መግለጫው አስታውቋል።

በሀገር አቀፍና በክልል ደረጃ የሴቶችና ሕፃናት ጾታዊ ጥቃትንና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ለመከላከልና ለማስወገድ ግብረ-ኃይል በማቋቋም እንዲሁም ሕክምና፣ የፍትሕ፣ የሥነ-ልቦና፣ ማኅበራዊና ሌሎች ድጋፍን የሚሰጡ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ተደራሽነት የማድረግ ሥራ ተሠርቷል።

ባለፉት ስድስት ወራትም የሕፃናትና የወጣቶችን መብትና ተጠቃሚነትን ማጎልበት፣ የማኅበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን በመዘርጋት ፣ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር መከላከልና ከስደት ተመላሽ ዜጎችን የማኅበራዊና ኢኮኖሚ አገልግሎት ተጠቃሚነትን ማሳደግ ሥራ እንደተሠራ በመግለጫው ላይ ተጠቅሷል ።

በቀጣይም አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን የሥራ እድል ፈጠራ ሥራዎችን በስፋት አጠናክሮ ማስቀጠል፣ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ማጠናከርና ውሎ እና አዳራቸውን ጎዳና ያደረጉ ዜጎች ሕይወት ለማሻሻል ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ ሥራዎች ለማጠናከር በትኩረት እንደሚሠራ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ገልጿል ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞኢ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ የሚስተዋሉትን መዋቅራዊና ተቋማዊ ችግሮች በመቅረፍ ...

መንግስት ከስንዴ ኤክስፖርቱ ጎን ለጎንም አጉራ ዘለል የሆነው፤ በዘላቂነት መዋቅራዊና ተቋማዊ ችግር የሚስተዋልበትን የግብይት ስርዓት በማያዳግም ሁኔታ መፍታት ይጠበቅበታል በስንዴ ምርት ላይ የመጣው እጅን በአፍ የሚያስጭን እምርታም በልኩ እውቅና ሊሰጠው ፤ አንድምታውንም ሰፋ አድርጎ መመልከት ይገባል።

ሉዓላዊነቷንና ነጻነቷን ጠብቃ ሳታስደፍር የኖረች ጥንታዊት ኢትዮጵያ። ቅኝ ያልተገዛች ብቸኛ አፍሪካዊት ሀገር። እስካፍንጫው የታጠቀን ቅኝ ገዢን ከአንድም ሁለት ጊዜ ድል ያደረገች። በጸረ ቅኝ ግዛት ትግሉ ቀንዲል የሆነች። የፓን አፍሪካኒዝምና የብላክ ኮንሸየስ ዋልታና ማገር ፤ የራሷ ፊደልና የዘመን አቆጣጠር ያላት ፤ የሚሉ እውነቶች ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በተነሱ ቁጥር አብረው የሚወሱ ቢሆንም ድህነቷ ፣ ኋላ ቀርነቷና በምግብ እህል ራሷን አለመቻሏና ተመጽዋችነቷ ጋርዶባት ፤ ጥላውንና አዚሙን ጥሎባት፤ አንጸባራቂ ገጽታዋን አጠልሽቶባት ይገኛል።

ድርቅና ርሀብ በተነሳ ቁጥር ስሟ አብሮ ይነሳል። በመዝገበ ቃላት ላይም ሆነ በሌላ መጽሐፍ ላይ የርሀብ ምሳሌ ሆና ስትጠቅስ ማንበብ ምን ያህል ቅስም ሰባሪና አንገት አስደፊ እንደሆነ ለኢትዮጵያውያን መንገር ለቀባሪ እንደማርዳት ነው። ተረጅነትና ተመጽዋችነት ሀገር ፊት ላይ ያለ አሸማቃቂ ለምጽ ነው። አይደብቁት አይሸግጉት ነገር ፊት ላይ ያለ የሀገር ለምጽ ነው።

የቦረናን ድርቅና ርሀብ ልብ ይሏል። ቢያንስ ላለፉት 50 አመታት ይህ ማንነቷ ኢትዮጵያንም ሆነ ዜጎቿን በሄዱበት እንደ ጥላ ሲከተል ኖሯል። ለለውጡ መንግስት ምስጋና ይግባውና በዓለም አደባባይ በኩራት ደረታችንን ነፍተን ፣ አንገታችንን ቀና አድርገን እንዳንራመድ ቀይዶ ይዞን የነበረው የተመጽዋችነት ሰንሰለት ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመበጣጠስ ከጫፍ ደርሰናል።

ባለፉት ጥቂት አመታት የተከናወኑ የአረንጓዴ አሻራ ፣ የኩታ ገጠም ግብርና ፣ የበጋ ስንዴ ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ፤ የሜካናይዜሽን ግብርና ፤ የህዳሴው 3ኛ የውሃ ሙሊትና 2ኛው ተርባይን ኃይል ማመንጨት መጀመር ፣ ወዘተረፈ. የሀገራችንን ተስፋ ከወዲሁ እያለመለመ ይገኛል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ ዞን የዱግዳና ቦራ ወረዳዎችን የመኸር የስንዴ ኩታ ገጠም እርሻን በጎበኙበት ወቅት ፤ በያዝነው አዲሱ ዓመት ስንዴን ለውጭ ሀገር ገበያ ለማቅረብ የተያዘው ግብ እጅግ ተስፋ የሚሰጥ ደረጃ ላይ ይገኛል ማለት ትልቅ ሀገራዊ ብስራት ነበር። እንዳሉት 38 ሚሊየን ኩንታል ወደ ውጭ የሚያስችል አቅም ተፈጥሯል። በመጀመሪያ ዙር ከሚላከው 3 ሚሊየን የተወሰነው መላክ ተጀምሯል። እንደ አለመታደል ሚዲያዎቻችን በነጠላ ዜና አለፉት እንጂ በሰበር ሊዘገብ ፤ ሆኖም ዛሬም አልረፈደምና ተገቢውን የሚዲያ ሽፋን ሊያገኝና እንደ ሀገር ሊከበር/ሴሌብሬት/ሊደረግ ይገባል።

ወደ ጠቅላይ ሚንስትሩ ንግግር ስመለስ ፤ ኢትዮጵያውያን በዚህ ልክ መስራታችን ብሔራዊ ክብራችን እና የሀገር ሉዓላዊነታችንን ከማስከበር ጋር በቀጥታ የተገናኘ መሆኑን ፤ የመንግስትም ዋነኛ ትኩረት ከዚህ በፊት የነበረውን ርሀብ የተፈጥሮ ሀብታችንና ያለንን ጉልበት በአግባቡ በመጠቀም ስንዴን ከሀገር ቤት ፍጆታ አልፈን ወደ ውጭ ወደ መላክ መቀየር እንደሆነ ፤ መሰደድን በሀገር ወደ መስራት መቀየር ፤ የመሬት መራቆትን ወደማልበስ ለማሸጋገር የመንግስት የትኩረት አቅጣጫ ተደርጎ እየተሰራ መሆኑን የምስራች ብለዋል። ባለፈው ዓመት በበጋ መስኖ 600ሺህ ሄክታር መሬት በማልማት 26 ሚሊዮን ኩንታል መመረቱን ፤ በአጠቃላይ የበልግን ሳይጨምር በመኸር 110 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ተመርቷል።

ይህ ታሪካዊ እመርታ የሀገራችንን ገጽታ ፣ ግብርናዊ ስሪትና የስነ ልቡና ውቅር የሚቀይር ወሳኝ መታጠፊያ/ክሪቲካል ጃንክቸር/ ነው። ለሌሎችም ሁለንተናዊ ኢኮኖሚያዊ ብልጽግና መስፈንጠሪያ ሆኖ ስለሚያገለግል በቀላሉ የሚታይ ስኬት አይደለም። በአጠቃላይ ሀገራችን ግብርናና አረንጓዴ ኢኮኖሚ የሰጠችው ትኩረት ፤ በአለማችን ላይ ከተከሰተው የአየር ጠባይ ለውጥ ፤ የዓለም ሕዝብ ቁጥር በእጅጉ እያሻቀበ በመምጣቱ የግብርና ምርት ውጤቶች በእጅጉ እየተፈለጉ ባለበት ወቅት ጋር መገጣጠሙ አለማቀፍ አንድምታ እንዲኖረው አድርጓል።

ያለንበት ዘመንም ሆነ መጪው ጊዜ ለግብርና ምቹ ነው። ለዚህ የሚበጅ የግብርና መሠረተ ልማት ግንባታ ላይ ትኩረት እንደተሰጠው ሁሉ ፤ ይሄን የሚመጥን የግብይት ስርዓት ፣ ተጠያቂነትና የሕግ የበላይነት በንግዱ ዘርፍ ተግባራዊ ካልተደረገ ምርትና ምርታማነት የቱንም ያህል ቢጨምር ገበያውን ማረጋጋትና ሸማቹንም አምራቹንም ተጠቃሚ ማድረግ አይቻልም። በዚያ ሰሞን በሲሚንቶ ሰሞኑን ደግሞ በስንዴ ግብይቱ የምናየው ችግር ለዚህ ጥሩ አብነት ነው። ስለዚህ አበክሮ ጎን ለጎን ሊሰራ ይገባል።

በተደጋጋሚ እንደምለው መጪው ዘመን ለግብርና ኢኮኖሚው ብሩህ እንደሆን እየተለፈፈ ይገኛል። አፍሪካም ሆነች ሀገራችን የሰፋፊ የእርሻ መሬቶች ፣ የተፈጥሮ ሀብት፣ የሰፊ ገበያ፣ በመልማት ያለ የሰው ኃይል፣ ...፤ እምቅ አቅም potential ያላቸው መሆናቸው አይን ማረፊያ አድርጓቸዋል። እ.አ.አ በ2050 የዓለም ሕዝብ ቁጥር 10 ቢሊዮን ይደርሳል ተብሎ ተተንብዮል።

የቻይናና የሕንድ ኢኮኖሚ እድገትን ተከትሎ የመሸመት አቅም መጎልበት ጋር ተያይዞ የሚያሻቅበው የምግብ ሸቀጦችን ፍላጎትን ለማርካት፤ በአመት ከ100 ትሪሊዮን ዶላር በላይ የሚያገላብጠው ግብርና የዓለም ኢኮኖሚ መሪነትን በቅርብ ከኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ይረከባል ተብሎ ስለሚጠበቅ፤ ትኩረቱ ባልታረሰው የአፍሪካ ድንግል መሬት ላይ መሆኑ ዘመኑን ይዋጃል። አገራችን ለግብርናውና ለአረንጓዴ አሻራ የሰጠችው ትኩረት ትክክለኛና ስትራቴጂካዊ ውሳኔ ነው።

የዓለም ሕዝብ ቁጥር እድገት አሁን ከሚገኝበት ሰባት ነጥብ አምስት ቢሊዮን፤ በክፍለ ዘመኑ መጨረሻ 11 ቢሊዮን ይደርሳል ተብሎ መተንበዩ፤ በዓለም በተለይ በቻይና፣ በሕንድና በሌሎች ታዳጊ አገራት እየተመዘገበ ካለው ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ጋር የምግብ ፍላጎት እጅግ ጨምሯል። እድገቱን ተከትሎ የመግዛት አቅም ከፍ በማለቱ እና የመጣው የአመጋገብ ለውጥ ፍላጎቱን አንሮታል። ባለፉት 20 እና 30 አመታት በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ቻይናውያን፣ ሕንዳውያን፣ ብራዚላውያን ፣ ኢንዶኔዢውያን፣ ማሌዢውያን፣ ወዘተረፈ ከድህነት ወደ መካከለኛ ገቢ ማደጋቸው በግብርና ውጤቶች ፍላጎት ላይ መሠረታዊ ለውጥ አምጥቷል።

በተቃራኒው የሚታረስ መሬትና የውሃ እጥረት እንዲሁም የአየር ንብረት ለውጥ በአናቱ ተጨምሮ ከአመት አመት ፍላጎቱን ማሟላት አዳጋች እያደረገው መጥቷል። የዓለም ሙቀት መጨመርና የደኖች መጨፍጨፍ፤ የአፈር መሸርሸርንና የመሬት መራቆት፣ በርሃማነት፣ ድርቅ፣ ሰደድ እሳት፣ ጎርፍ የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚውን እያሽመደመደው ነው። በዚህ የተነሳ ፍላጎቱንና አቅርቦቱን ማጣጣም ከጊዜ ወደ ጊዜ አዳጋች እየሆነ መጥቷል። እንደ ኮቪድ 19 ያለ የተፈጥሮ አደጋ ሲከሰት ደግሞ ችግሩ ከፉኛ ይባባሳል።

የዓለም የምግብና የእርሻ ድርጅት ቀደም ባለ ጊዜ ይፋ እንዳደረገው ከወረርሽኙ ጋር በተያያዘ 265 ሚሊዮን ሕዝብ ለከፋ የምግብ እህል እጥረት ተዳርጓል። ከባድ ውሽንፍር፣ የጎርፍ መጥለቅለቅ፣ ድርቅ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ ዓይነት የተፈጥሮ አደጋዎች በተከሰቱ ቁጥር የምግብ እህል እጥረት ከፍ ሲልም ርሀብ ይከሰታል። በመላው ዓለም አንድ ቢሊዮን ሕዝብ በምግብ እጥረት ሳቢያ ለተለያዩ የጤና እክሎች ተዳርጓል።

ወደ አገራችን ስንመጣ 47 በመቶ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን የከፋ የምግብ እጥረት እንዳለበት መረጃዎች ያትታሉ። ከወረርሽኙና ከድርቅ ጋር ተያይዞ ባለፈው ወደ 30 ሚሊዮን የሚጠጋ ወገናችን ለምግብ እህል እጥረት መጋለጡን መንግሥት ይፋ አድርጓል። ግብርና ለአገሪቱ ጥቅል ብሔራዊ ምርት ድርሻው 47 በመቶ ቢሆንም እድገቱ የሚጠበቀውን ያህል አይደለም።

አገራችን የወጣት ፣ 85 በመቶ የሚሆነው ሕዝቧ በገጠር የሚኖር፣ አመቱን ሙሉ የሚፈስሱ ወንዞች፣ የሁለት ጊዜ የዝናብ ወቅት፣ የሚታረስ ሰፊ መሬት፣ ታታሪ ሕዝብ ያላት እና ቀደምት ከስድስት ሺህ አመታት የሚሻገር የእርሻና የግብርና ታሪክ ያላት ምድር ብትሆንም ራሷን እንኳ በቅጡ መመገብ አልቻለችም።

በስንዴውና በዘይቱ ሲገርመን ሽንኩርትና ምስር ከውጭ እያስገባን ነው። በእኛው አባይ የለማ የግብጽ ብርቱካን በአለፍ ገደም ብቅ እያለ ነው። ካለፉት ሦስት አመታት ወዲህ ግን ከዚህ አዙሪት ለመውጣት በመንግሥት በኩል ፍላጎትና ቁርጠኝነትን እየተመለከትን ነው። ዛሬም ተረጂ ፣ ዛሬም ስንዴና ዘይት ከውጭ አስመጪ መሆናችን ቁጭት የፈጠረ ለለውጥ ያነሳሳ ይመስላል።

ቀድሞውኑም በኢኮኖሚያዊ አዋጭነትና በጥናት ባልተመሠረተ አግባብ ግብርናው የሚገባውን ያህል ድጋፍ ሳያገኝ ከፈረሱ ጋሪው እንዲሉ በግዕብታዊና በፖለቲካዊ ውሳኔ የዩኒቨርሲቲና የኢንዱስትሪ ፓርክ መዓት አግተልትለን ለምሩቃኑ ሥራ ለፋብሪካው ጥሬ ዕቃ ማቅረብ አልቻልንም። ለዚች አገር ነፍስ መዝሪያዋም መሞቻዋም ግብርና ነው።

ግብርና ላይ ከተሳካልን ሌሎችን ዘርፎች ይዞ መነሳትና መውጣት ይቻላል። ለቀደሙት 27 አመታት ከፕሮፓጋንዳ ባለፍ የአገራችንን ስነ ምህዳር ታሳቢ ያላደረገ የዘመቻ ሥራ መሠራቱ ዛሬ ላይ ጥሎናል። ቆም ብለን ትንፋሽ ስበን የመጣንበትን መንገድ ገምግመን በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ የሚስተዋለውን መዋቅራዊና ተቋማዊ ችግር ቀርፈን ትኩረታችን ግብርናው ላይ ሊሆን ይገባል።

ይህ እስኪሆን የለውጥ ኃይሉ እጁን አጣጥፎ አለመቀመጡና የህልውናችን መሠረት የሆነውን አየር ንብረታችን እንዲያገግም በአምስት አመታት ውስጥ ወደ 25 ቢሊዮን ችግኝ ለመትከል ግብ ጥሎ ካለፉት አራት አመታት ጀምሮ ወደ ተግባር መገባቱ የኑሮአችንና የኢኮኖሚያችን የጀርባ አጥንት ለሆነው ግብርና መልካም ዜና ነው። በሚቀጥሉት አምስትና አስር አመታትም የአገራችንን አየር ንብረትና ሥነ ምህዳር / ኢኮሎጂ / ፍጹም ይቀይረዋል።

ይህ በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ላይ ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት መስፈንጠሪያ ነው። ይህ በሂደት እውን እስኪሆን የለውጥ ኃይሉ ስንዴን ከውጭ ማስገባትን ለማስቀረት፣ ግብርናውን ሜካናይዝድ ለማድረግ፣ መሬት ጦም እንዳያድር፣ የኩታ ገጠም አሠራርን ለማስፋፋት የሚያደርገው ጥረት ይበል የሚያሰኝ ሆኖ ወጥ በሆነና ስፋት ባለው አግባብ እንደየ ሥነ ምህዳሩ በመላ አገሪቱ ተግባራዊ ማድረግ ላይ ግን ይበልጥ ሊሠራ ይገባል።

እንደ አገር ያለን ሀብት የሚታረስ መሬት፣ ውሃና የሰው ኃይል ነውና ለግብርናው ቅድሚያ ሰጥተን ልንረባረብ ይገባል። ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረግ ሽግግር ያለ ግብርናው ጽኑ መሠረት እውን ሊሆን አይችልምና። ስለሆነም ያለንን ሀብት ሁሉ አቀናጅተን ግብርናው ላይ ልንረባረብ ይገባል። የአረንጓዴ አብዮት በማቀጣጠል አንገታችንን ሲያስደፋን ሲያሸማቅቀን ከኖረው ርሀብ፣ ቸነፈርና ድህነት ይህን ተከትሎ ከማይለየን ተረጂነት መላቀቅ አለብን።

ሻሎም ! አሜን ።

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# ‹‹የኢትዮጵያን እውነታ ማስረዳት ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአሜሪካም ጥቅም አለው››

- አቶ ዳንኤል ነቢዩ
ወጣቱ ዲያስፖራ

ጽጌረዳ ጫንያለው

**‹‹አብረን ስንሆን እናምራለን፤ ኢትዮጵያችንም ከፍ ትላለች፡፡ ድምቀትና ውበታችን ይጎላል፡፡ የተሻልን ለመሆንም የሚያግደን ነገር አይኖርም፡፡ ምክንያቱም በሀሳብ፣ በፍላጎት፣ እና በአላማ እንመሳሰላለን፡፡ በእውነት ቆመን ውሸቶችን እንቀብራለን፡፡ ወደ ስኬት ለማምራትም መንገድ እንጠርጋለን፡፡‹‹ የሚል እምነት አለው ‹‹አብረን›› የሚል ድርጅትና ዌብሳት ከጓደኞቹ ጋር በማቋቋም ሀገሩንና ወገኑን ለመጥቀም ሲንቀሳቀስ የቆየውና በእዚህ ተግባራቸው እንደሀገር እውቅና ከተሰጣቸው ዲያስፖራዎች መካከል የሆነው ዳንኤል ነቢዩ፡፡**

**በእርሱ አስተሳሰብ በግል እንቅስቃሴ ብቻ የሚመጣ ለውጥ የለም፡፡ ተፈጥሮ እንኳን ካልተደጋገፈች መቆም አትችልም፡፡ ስለዚህም እንደሰው ሁለት እና ከዚያ በላይ ሆኖ መሥራት ግድ ያስፈልጋል፡፡ የጋራ ግብን በቀላሉ ለማሳካትም ያስችላል፡፡ ዛሬ በጦርነትና በሁከት ውስጥ ያልቆየነው ተባብረን ችግሮችን መፍታት በመቻላችን ነው፡፡ የተጎዱትን ሕይወት ለማስቀጠል የቻልነውም እንዲሁ በአንድነት ቆመን ለእነርሱ መድረስ ስለቻልን ነው፡፡ ስለዚህም መተባበር ቅድሚያ የሚሰጠው ነገር እንደሆነ ሁሉም ሊያውቀው ይገባል ባይ ነው፡፡ ታዲያ ይህ አቋሙን እንዴት እየተገበረው ነው፤ ከእርሱ የሚወሰደውስ የሕይወት ልምድ ምንድነው ካላችሁ በዛሬ የሕይወት ገጽታ አምዳችን ይህንን እናስቃኛችኋለን፡፡ መልካም ንባብ!!**



ፎቶ- እዮብ ተፈሪ

### የሀገር ልጅ የማር ጠጅ

ዳንኤል የተወለደው አዲስ አበባ ከተማ ነው፡፡ እስከ 10 ዓመቱ ድረስም በሀገሩ ከእኩዮቹ ጋር ሲቦርቅ አድጓል፡፡ በተለይም በሾላ አካባቢ ያላደረገው ነገር አልነበረም፡፡ የሀገሩን ፍቅር በሚገባ የተማረበት ጊዜ ይህ እንደነበርም ያስታውሳል፡፡ ስለዚህ በሀገሩ ማንነቱ የተገነባበት ጊዜ እስከ 10 ዓመቱ ያለው እድሜው ነው፡፡ በእርግጥ ለማንኛውም መሰረቱ ይህ እድሜ እንደሆነ ይታሰባል፡፡ የማይረሱና የሕይወታችንን ትልቁን አሻራ የሚጥሉበት የእድሜ እርከን ቢኖር የልጅነት ወቅት እንደሆነ ማንም አይዘነጋውም፡፡ ስለሆነም ይህንን እድሜውን በሚገባ በሀገሩ ኖሮበታል፤ ተምሮበታል፡፡ የቀጣይ ስንቁንም ይዞበታል፡፡

ማንበብ አጥብቆ የሚወድ ልጅ የሆነው በሀገሩ ሳለ ነው፡፡ የሀገሩን ታሪክ መስማትም እንዲሁ ይወዳል፡፡ አገርን ለማወቅ ደግሞ አባቱ መሰረት ሆነውለታል፡፡ ድክድክ እያለ ከአባቱ ጋር ተያይዞ ከተማዋን እንዲያካልል ያደርጉታል፡፡ በዚያ ላይ የስነ ጽሁፍ ችሎታ እንዲኖረውም መሰረት ጥለውለታል፡፡ ማለትም አባቱ ነቢዩ ኢያሱ ጋዜጠኛ ነበሩና የእርሳቸውን ፈለግ እንዲከተል በብዙ አስተምረውታል፡፡

ከጋዜጣ ላይ ጽሁፋቸው ውጪ መጽሐፍትን ይጽፉሉና ማንበብን እንዲወድም አስችለውታል፡፡ እናም በቀላሉ አንባቢ ፣ ጸሐፊና ታሪክ አዋቂ እንዲሁም ሀገሩን ወዳድ እንዲሆን በአስተዳደጋቸው ቀርጸውታል፡፡ ጠዋት ወጥተው ማታ ቢገቡም ለእርሱ ፍላጎት ግን ቦዝነው አያውቁምና አዋቂም አድርገውታል፡፡

ዳንኤል ሩጫ ላይ ልዩ ፍላጎት ያለው ልጅ ነው፡፡ እንደውም ከዚህ ጋር ተያይዞ ቅጽል ስም ወጥቶለታል፡፡ ‹‹ንፋስ›› የሚል፡፡ ምክንያቱም ማንም አይቀድመውም፡፡ ሁልጊዜም ትምህርት ቤቱን ተወዳድሮ በማሸነፍ ያስጠራል፡፡ ስለዚህ ከአባቱ ሲለይ ትምህርት ቤት ላይ ከእኩዮቹ ጋር ቀዳሚ ጨዋታዎቹ ሩጫና እግር ኳስ ነበሩ፡፡

ለቤቱ የበኩር ልጅ የሆነው ዳንኤል፤ በብዙ መልኩ እገዛ ይደረግለታልና በነጻነት ያደገ ልጅ ነው፡፡ በዚህ ደግሞ ዳንኤል ልዩ ባህሪ እንዲኖረው አስችሎታል፡፡ ይህም ከሰው ጋር በቀላሉ የሚግባባና ቸር እንዲሆን በር ከፍቶለታል፡፡ አባቱ ለሥራና መሰል ጉዳዮች ወደ ውጭ ሀገር ሲሄዱ የተለያዩ መጫዎቻዎችን ያመጡለታል፡፡ ውጭ ያሉ ቤተሰቦቹም እንዲሁ ይልኩለታል፡፡ እናም ይህንን መጫወቻ ብቻውን አይጫወትበትም፡፡ ከጓደኞቹ ጋር ይጋራዋል፡፡ አለፍ ሲልም በቤት ውስጥ ሌላ መጫወቻ ካለው ለሌላቸው ይሰጣል፡፡ ይህ ባህሪው ደግሞ ዛሬ ድረስ የተቸገሩትን አይቶ እንዳያልፍ አድርጎታል፡፡

ዳንኤል ነጻ ሆኖ በማደጉ ተግባቢ አድርጎታል፡፡ አሁን ለተቸገሩት አካባቢዎች ለመድረስም የቻለው በዚህ መነሻነት ነው፡፡ የዳንኤል የልጅነት ህልም ብዙ ነው፡፡ በየጊዜውም ይቀያየርም ነበር፡፡ በተለይም ከ10 ዓመቱ በኋላ የነበረው የልጅነት ሕይወት የትውልድ ሀገሩን ትቶ ሀገረ አሜሪካን የተቀላቀለበት ስለነበር ምርጫዎቹን ብዙ አድርገውታል፡፡

አዲስ አየር፣ አዲስ ማህበረሰብና የአኗኗር ዘዬ በራሱ መልመድ ሀሳብ አስቀያሪ እንደሆነ ይታመናል፡፡ እናም እርሱም የዛሬ ሕልሙን ለነገ መድገም ያልቻለው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ አንድ ያልቀየረው ነገር ቢኖር ስለሀገሩ የነበረውን አመለካከት ብቻ ነው፡፡

ዳንኤል ሀገሩን ትቶ ወደ አሜሪካ የሄደበት ምክንያት አባቱ ከመንግስት ጋዜጠኝነት ሥራቸው ወጥተው በግል ጋዜጦች ላይ ይሰሩ ነበርና በወቅቱ የግሎቹ ሚዲያዎች ሲዘጉ ስራቸው ስለተቋረጠ ሀገራቸውን ትተው ቤተሰቡን ይዘው እንዲሄዱ ተገደዱ፡፡ በዚህም ልጅ ዳንኤልም ብቻውን ምርጫ የለውምና አብሯቸው ነጎደ፡፡ አሜሪካ ሌላኛው ዓለም ሆናለት ዛሬ ድረስ ዘለቀ፡፡

ዳንኤል አሜሪካ ቢሄድም ምንም የጎደለበት ነገር አልነበረም፡፡ ምክንያቱም ቤተሰቡ ከእርሱ ጋር ነው፡፡ በዚያ ላይ ትንሽ ልጅ በመሆኑ ሁሉንም ለመላመድ አይቸገርም፡፡ ከሁሉም በላይ በኢትዮጵያዊያን ነጻነት በማደጉ የፈለገውን እያደረገ እንዲኳዝ ሆኗል፡፡ አንድ ነገር ግን ዛሬ ድረስ አይረሳውም፡፡ እንዲህ ያስታውሰዋል ‹‹ኢትዮጵያ ውስጥ በነጻነት መጫወት አለ፡፡ ለምሳሌ፡- ሹሌ የሚባል የድብድብ መልክ ያለው ጨዋታ ነበር፡፡ ደስተኛ ሆነን የምንጫወተውም ነው፡፡ ከሁሉም ጨዋታዎች እንመርጠው ነበር፡፡ እናም ያንን ልምዴን ይዤ አሜሪካ ልከውነው ሞከርኩ፡፡ ሆኖ ሁሉም ነገር ውበት የሚኖረው በሀገር ስለሆነ እንዳሰብኩት አላስደሰተኝም፡፡ ባለማወቅ እንጫወት ብዬ ከልጆቹ ጋር ስደባደብ ወዲያው ተያዝኩና ተመታሁ፡፡ ይህንን ሳስብ የጨዋታ ነጻነት ሀገሬ ውስጥ ብቻ ያለ ይመስለኛል›› ይላል፡፡

ዳንኤል ሌላው ልጅነቱና ሀገር ወዳድነቱን ሲያነሳ አንድ ነገር ላይ ያሰምራል፡፡ ይህም ሀገርኛ ቋንቋን ማወቅ ላይ ሲሆን፤ የቤተሰብ መልካም ተጽዕኖ ብዙ ነገሮችን እንዳስተካከለለት ይናገራል፡፡ ‹‹ብዙዎች እንግሊዝኛን እንጂ አማርኛን እንዲናገሩ አያበረታቱም፡፡ የውጭ ቋንቋ ብቻ መሰረታዊ ነገር እንደሆነ ያምናሉ፡፡ ይህ ደግሞ ባህላቸውን ጭምር እንዲረሱ ያስገድዳቸዋል፡፡ ውጭ ሀገር ያሉ አብዛኞቹ ኢትዮጵያንም በዚህ መስመር ውስጥ ናቸው፡፡ ቤተሰብ እንጂ እነርሱ ሀገርኛ ቋንቋን አይናገሩም፡፡ እኔ ግን አቀላጥፌ እንድናገር ሆኛለሁ፡፡ ከብዙዎች ጋር ተግባብቼ ለሀገሬ ማድረግ ያለብኝን እንድከውን ያስቻለኝም ይህ እድል ነው፡፡ ስለዚህ ቤተሰብ ቢያስብበት መልካም ነው ማለት እፈልጋለሁ፡፡›› ይላል፡፡

### ከአዲስ አበባ እስከ አሜሪካ በትምህርት

ምስካዬ ኅዙናን ትምህርት ቤት ሲማር ማርክ ባይኖረውም መጽሐፍ የሚያነቡለትን አንድ አባት ፈጽሞ አይረሳቸውም፡፡ ምክንያቱም ታሪክ አዋቂ አድርገውታል፤ ማንበብን እንዲወድ ከአባቱ ቀጥሎ መሰረት ጥለውለታል፡፡ ከዚያ ባሻገርም ኢትዮጵያዊነትን እንዲያጣጥመውና እንዳይረሳውም አስችለውታል፡፡ በተለይ ይህ የንባብ ጊዜ እንደ ትምህርት ለተማሪዎች የሚቀርብ በመሆኑ ሁሉንም ትምህርትን ወዳድ ያደረገ እንደነበር ያነሳል፡፡ ክፍለ ጊዜውን እንደ ልዩ መዝናኛ ቆጥረውትም ነው የሚከታተሉት፡፡

አሁንም እንዲህ አይነት ልምዶች ያስፈልጋሉ ባይ ነው፡፡ ምክንያቱም የተማሪውን ስነምግባር ከማነጽ ባለፈ ሀገር ወዳድነት በእያንዳንዱ ተማሪ ልብ ውስጥ እንዲኖር ያደርጋል፡፡ በተመሳሳይ በእውቀት የሚማር ተማሪን ይፈጥራል፡፡ የዛን ጊዜ ተማሪዎች ቀለምን በቶሎ የሚይዙ፤ እውቀትን በአግባቡ የሚጨብጡና ለተግባር የሚተጉ የሆኑት እንዲህ አይነት ገንቢ ትምህርቶች በማርክ ተታለው ሳይሆን ተወደው ስለሚሰጡ እንደሆነም ከተሞክሮው በመነሳት ያብራራል፡፡

‹‹እንደነዚህ አይነት ትምህርቶች ጠያቂ ትውልድንም ያፈራሉ፤ መናገርን የሚያበረታታ እንዲሁም ምን አይነት ምልከታ እንዳለን የሚያሳይ በመሆኑ መልካም አስተሳሰቦችን ከአዕምሯችን የማይወጡ ነገሮችን ያስቀምጣሉ፡፡ ይህ ሆነ ማለት ደግሞ ተማሪዎቹ የትም ሀገር ላይ ቢሆኑ የማይረሷትን ሀገር ይሰጣቸዋል፡፡ ለሀገራቸው ልማት የሚተጉ ዜጎችም መሆን ይችላሉ፡፡ » ይላል ዳንኤል በትምህርቱ ያገኘውን ጥቅም ሲያስረዳ፡፡

ዳንኤል ኢትዮጵያ ሳለ የተማረው አንድ ትምህርት ቤት ብቻ ነው፡፡ ይህም ምስካዬ ኅዙናን ትምህርት ቤት ሲሆን፤ እስከ አምስተኛ ክፍል የተከታተለበት ነው፡፡ ከዚያ ስድስተኛ ክፍልን መቀጠል የቻለው ሌላኛውን የእድገት ደረጃ በቀጠለበት ሀገረ አሜሪካ ነው፡፡ እንግሊዝኛና ሒሳብ ትምህርቶችን ተፈትኖ ካለፈ በኋላ ከቤት ብዙም ሳርቅ በሚገኘው ሆምሲ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ከስድስተኛ እስከ ስምንተኛ ተከታትሏል፡፡ ከዚያ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ደግሞ በሮበርት ኢሊ ትምህርት ቤት አጠናቋል፡፡

የዩኒቨርሲቲ ትምህርቱን ደግሞ ራድፎርድ ዩኒቨርሲቲ የተከታተለ ሲሆን፤ በባዮ ኬሚስትሪ የትምህርት መስክም የተመረቀበት ነው፡፡ ከዚያ ጆርጅ ሜሶን ዩኒቨርሲቲ በመግባት ሁለተኛ ዲግሪውን በፉድ ሴኩዩሪቲ ተማረ፡፡ ሌላም ሁለተኛ ዲግሪ ከዚሁ ዩኒቨርሲቲ በትምህርት ያገኘ ሲሆን፤ ይህም ኢኮኖሚክስና ኢንተርናሽናል ቢዝነስ ነው፡፡

ዳንኤል በንብረት ስጋት አስተዳደር ትምህርት መስክም ሰርተፍኬት ከቼሳፔኬ ሪጅናል ሴኪዩሪቲ አግኝቷል፡፡ በተመሳሳይ እኤአ በ2013 የአደጋ ትንተና ላይ ትኩረቱን ያደረገ ትምህርት ተምሮ ሰርተፍኬት ማግኘት ችሏል፡፡ የምግብ ደኅንነት መከላከያና መቆጣጠር ላይም ስልጠና ወስዷል፡፡ ዛሬም ቢሆን ምንም እንኳን በተመራማሪነትና በሥራ ልምድ የተለየ እውቀት እያካበተ ቢሆንም መማሩ ላይ ግን ገደብ መጣል አይፈልግም፡፡ የሁልጊዜ ተማሪ መሆንን ይመርጣል፡፡

### ሥራ በአሜሪካ

ከቤተሰቡ የተላቀቀው የውጭው ዓለም እንደሚያደርገው በ18 ዓመቱ ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲ በመግባት አራት ዓመታትን ከተማረ በኋላ ደግሞ በ23 ዓመቱ ሥራን አሀዱ ብሏል፡፡ የመጀመሪያ መስሪያ ቤቱ የዩናይትድ ስቴትስ የምግብ እና የመድኃኒት አስተዳደር ሲሆን፤ በረዳት ተመራማሪነት የሰራበት ነው፡፡ እኤአ 2008 እስከ 2010 የሰራ ሲሆን፤ ከሦስት ዓመት የሥራ ላይ ቆይታ በኋላ ደግሞ ወደ ምግብ ካምፓኒዎች ገባ፡፡

በምግብ ኢንዱስትሪው ውስጥ መነሻ መስሪያ ቤቱ ‹‹ዲን ፉድ›› የሚባል ድርጅት ሲሆን፤ በጥራት ማረጋገጥ ውስጥ ኃላፊነት ወስዶ ሦስት ዓመት ያገለገለበት ነው፡፡ ቀጣዩ የሥራ ቦታው ደግሞ ‹‹ቱልኮፍ›› የምግብ ምርቶችን የሚያመርት ካምፓኒ ሲሆን፤ እዚህም ልክ እንደ ላይኛው በጥራት ማረጋገጥ ላይ ሰርቷል፡፡ ቆይታው ግን ከአንድ ዓመት አልዘለለም የተሻለ ፍለጋ ወደ ሌላ ካምፓኒ

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ



ተዘዋውሯል:: ይህም ‹‹ፉችስ›› የሚባል ድርጅት ሲሆን፤ ሰሜን አሜሪካ ውስጥ የሚገኝ ካምፓኒ ነው:: የደህንነት እና ስጋት አስተዳዳር ላይ በኃላፊነት ሰርቶበታል:: ቆይታው አምስት ዓመታትን የዘለቀ ነው::

ከአንድ ዓመት ያልዘለለ ቢሆንም ‹‹መኮርሚክ›› የተሰኘ ካምፓኒ ውስጥም እንዲሁ የጥራት ተቆጣጣሪ በመሆንም አገልግሏል:: በተመሳሳይ ግሪን ታምፕ ኢንዱስትሪ ውስጥም እንዲሁ በጥራት ተቆጣጣሪነት ዓመት ያህል በሥራ ቆይቷል:: በስተመጨረሻ መዳረሻውን ያደረገውና እስካሁን ድረስ የሰራበት ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተዋቂ የሆነው ‹‹ኔስሌይ›› የተሰኘ ድርጅት ውስጥ ነው:: ይህ ድርጅት እንደ ኒዶ አይነት ምርቶችን የሚያመርት ሲሆን፤ ዓለም አቀፍ የንግድ ተንታኝ በመሆን አገልግሎበታል::

ዳንኤል አሁን ረፍት ወስዶ ይገኛል:: ሀገሩ ላይ መጥቶ የሀገሩን ልጅ አግብቶ አዲስ ሙሽራ ሆኗል:: በዚህ ቆይታው ደግሞ ብዙ ነገሮችን አይቶ ተመልሶ ለኢትዮጵያ የተሻለ ነገር ለመስራት አስቧል:: በተለይም ሙያውንና የሥራ ልምዱን በአጣመረ መልኩ ሀገሩን ለመጥቀም አልሟል:: በቆይታው ሥራዎችን ለመረዳት ጊዜ ያለው ይመስለዋል:: እስከአሁን ያያቸውም ነገሮች መኖራቸውን አጫውቶናል::

ሀገራችን ደግሞ በተለይም በኢንዱስትሪው መስክ የሚሰማራና የኢንዱስትሪ ምርቶችን በሙያው በጥራት የሚያመርት ሰውን አጥብቃ እንደምትሻ ምንም ጥርጥር የለውም:: ምክንያቱም በሀገር ውስጥ ጥራት ያለው ምርት ባለመመረቱ የመድኃኒትና ቁጥጥር ባለስልጣን በየጊዜው ኤክስፓይርድ ያደረጉ ናቸው፤ በጥራት አልተመረቱም እያለ የሚያቃጥላቸውን ምርቶች በርካታ ናቸው:: ይህንን ለማስቆምም ምርቶች እንደሀገር ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ ጭምር እየፈቀደች ነው:: እንደ ዳንኤል ያሉ ሀገር ወዳድና በሙያቸው ልስራ የሚሉ ዲያስፖራዎች ሲመጡ እሰየው እንጂ እንቢ የሚል አካል ይኖራል ተብሎ አይታሰብም:: ግድ ያስፈልጉናልና እንጠቀምባቸዋለን:: ለሕጻናት ተስፋ፤ ለሀገር የወጪ ቅነሳ በሙያተኞች የተመረተ ምርት እጅጉን ያስፈልጋል:: ስለዚህም ዳንኤል ጥራቱን የጠበቀ ምርት በሀገር ውስጥ እንዲመረትና ከውጭ የሚገቡትም ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ሙያውን ለሀገሩ ለማበርከት ዕቅድ አለው::

**‹‹አብረን›› የተሰኘ ድርጅት ማቋቋም**

አብረንን የተባለው ተቋም በዳንኤልንና ጓደኞቹ የተቋቋመ ነው:: ድርጅቱ ሲመሰርት ለሀገር ያለውን ዋጋ በሚገባ ተረድተውታል:: አመሰራረቱም ይህንን የተረዱትን ለመተግበር በማለም ነው:: ከሁለት ዓመት በፊት የጀመረ ሲሆን፤ መነሻ ምክንያቱ የውጭ ጫናውን መመከት ላይ ያነጣጠረ ነው:: በተለይም በሚዲያ ጫናው በኩል ያለውን ወገንተኝነት ለማስቆም ሁለገብ ሥራ ለመከወን አስበው ነው የገቡበት:: በዚህም እውነት እንዲገለጥ አድርገዋል:: በማቀናጀት ሀሳብን ማስቀየር ችለዋል:: የሀገርን ሉዓላዊነት የሚጻረሩ የሀሰት ዜናዎችን እያጋለጡም የኢትዮጵያን እውነተኝነት ለዓለም ሕዝብ አሳይተዋል::

መጀመሪያ አካባቢ የሚዲያው ወገንተኝነትና ጫና ሲበረታ እኛ ምን እናድርግ በሚል ሕጋዊ እውቅና ሳያገኙ በራሳቸው ፔጅ በኩል ሲንቀሳቀሱ ቆይተዋል:: ሆኖም የሀሰት ወሬው ሲፋፋምና ሀገር ላይ የሚደርሰው ጫና ሲበረታ በዚህ መልኩ መጓዛቸው ለውጥ ሊያመጣላቸው እንደማይችል አመኑ:: ስለዚህም ሰብሰብ ብለው በሕጋዊ መንገድ መንቀሳቀስ እንዳለባቸው ወሰኑ:: ‹‹ አብረን›› የሚል በአሜሪካ ሕጋዊ እውቅና ያለው ዌብሳይትም በመክፈት ትግላቸውን በይፋ አጧጧፉት:: ይህ ግን ያሰቡትን ያህል አላስኬዳቸውም:: ምክንያቱም ጀማሪዎች በመሆናቸው ተቀባይነታቸው ዝቅተኛ ነው:: እናም ሊያግዛቸው ወደሚችል አካል ጠጋ እያሉ መስራታቸውን ቀጠሉ:: ተዋቂና ተሰማሚ የሆኑ አካላትን በመጋበዝ ተአማኒነታቸውን ወደ መጨመሩም ገቡ:: ለዚህ ደግሞ የአሜሪካ ተወላጅና ዜጋ መሆናቸው በእጅጉ ጠቅሟቸዋል::

ሥራቸው ፖለቲካዊ ወገንተኝነት የሚያንጸባርቅ አለመሆኑም እንዲሁ በአሜሪካ ካሉ ተሰሚነት ካላቸው ሚዲያዎች ቀጥሎ ተቀባይነት እያገኙ መጡ:: የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የሚጻረሩ አካላትን በእውነታው መሞገታቸውና ማሳያ መጥቀሳቸውም ለተአማኒነታቸው እድል የሰጠ ነበር::

የጀመሩት ሰባት ልጆች በመሆን ነው:: የኢትዮጵያን እውነታ እያሳዩና ተቀባይነታቸው እየሰፋ ሲሄድ ግን ተከታያቸው በዛ:: ይህን ጊዜ ተጨማሪ ሥራዎችን ወደ መከወኑም ገቡ:: ይህም ዲፕሎማሲያዊ አገልግሎት ሲሆን፤ በዲጂታል፣ በሶሻልና በአካል እየተገናኙ ፐብሊክ ዲፕሎማሲው ላይ የቻሉትን ሁሉ አደረጉ:: ይህ ደግሞ ብዙ ለውጦችን እንዲያመጡ አስችሏቸዋል:: ለአብነት ከሕዝብ ተወካዮች ጋር በመነጋገር ሀሳብ ለዋጭ ተግባራትን መከወን ችለዋል:: ኢትዮጵያንን እርስ በእርስ እንዲያስተሳስሩም ሆነዋል::

ዳንኤል እንደሚለው ብዙ ጊዜ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ጣልቃ የሚገባው ሀሳቡን ካለመረዳት በመነጨ ነው:: የሚያምኗቸው ሚዲያዎች የሚያወሩት የሀሰት ዜናን ተከትለው ውሳኔ ለማስተላለፍ ይሰበሰባሉ:: የሚሟገታቸው ካጡም ወስነው ይወጣሉ:: እናም ይህንን ለመስበር በሁለት መልኩ ድርጅቱ ይሰራ ነበር:: አንድም የወከላቸውን የሕዝብ ተወካዮች በማነጋገር አለያም ራሳቸው ተመራጮችን ወደ ስብሰባው በመላክ ነው:: እናም በተደጋጋሚ ይህ ተግባር በመከወኑ ብዙ ስብሰባዎችን ፉርሽ እንዲሆኑ ማድረግ ችለዋል::

‹‹ብዙ ሚዲያዎች ሙሉ መረጃ ሳይኖራቸውና ለተለየ አላማ ቀንጭብ አድርገው ሀሳቦችን ለአሜሪካ ሕዝብ ያቀርባሉ:: የተሳሳተውን ሀሳብ በመያዝ ሕዝቡም ወደ አልተፈለገ መንገድ እንዲጓዝ ይሆናል:: እናም ይህንን ማቅናት ያለብን እኛ እንደሆነን ተሰማን:: እናም ኢትዮጵያ ላይ የተፈጠረውን ጫና ሙሉ ለሙሉ ማስቆም ባንችልም ያለው እውነታ እንዳይጠፋ ጠጠር መወርወር ጀመርን›› ይላል ባለታሪካችን::

በአሜሪካ ያሉ ሚዲያዎች በገንዘብም ሆነ በተሰሚነት ማንም ሊገዳደራቸው አይችልም:: እናም ይህንን እያወቁ ነበር ትንሿ ሻማ ምን ያህል ቀልጣ ብርሃን እንደምትሰጥ አምነው አብረን በሀገረ አሜሪካ ተአማኒ እንዲሆን ያደረጉት:: ሌላው በአብረን መሰባሰባቸው ወጣቱን እንዲይዙት አግዟቸዋል:: ዲያስፖራውንም ለሀገሩ እንዲደርስ አድርገውበታል:: በተጨማሪ ዲያስፖራው የኢትዮጵያ ኃይል እንደሆነም አሳይተውበታል:: በተለይም መሰረታዊ በሚባሉ የኢትዮጵያ ጥቅሞች ላይ ቸልታ ሳያሳዩ እንዲተጋገዙ በማድረግ በኩልም ብዙ ለፍተዋልና ከብዙ በጥቂቱ ተሳክቶላቸዋል::

የእውቀት ክፍተቱናን በሜኒስትሪም ሚዲያው መሸወድ ያጋጥም ስለነበር እርሱን የማጥራት ሥራ ሰርተዋል:: በተለይ የተማሩና ትልልቅ ቦታ ላይ ያሉ ዲያስፖራዎችን በመያዝ በኩልም የተሻሉ ነበሩና ለውጥ አምጥተዋል:: በተመሳሳይ በአብረን ዌብሳይት ላይ ትልቅ ታይም ላይን አስቀምጠው በየቀኑ የሚሞግቱበትን እድል ፈጥረዋል:: ይህ ደግሞ ከኢትዮጵያ ታላቁ ሕዳሴ ግድብ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ተቃራኒ ሀሳቦችን፣ ከጦርነቱ ጋር ተያይዞ የሚነሱ የሀሰት ዜናዎችን በመረጃ ለመሞገት ያስቻላቸው ነው::

ዊኪፒዲያ ላይ ሳይቀር ታሪክ ተሰርዞ ወቅታዊና የተሳሳቱ ታሪኮችን እስከ ማስቀመጥ የደረሱ ዘመቻዎች በኢትዮጵያ ላይ ተደርገዋል የሚለው ዳንኤል፤ በአብረን ይህንን ጭምር የመሞገት ሥራ ተሰርቷል ይላል:: ይህንን የሚያደርጉበት ሁኔታ ደግሞ ድሮ የነበረውንና የወጣውን መረጃ በማሳየት ነው:: አውቀው እንደሆነና በአሻጥር እንደሚከውኑት በማስረጃ በማስደገፍ ያብራራሉ፤ በቀጣይም ይህንን ያደርጋሉ:: ይህ ደግሞ ኢትዮጵያን ከተሳሳተ ትርክት ጠብቋታል ብለው ያምናሉ::

በአብረን በአሜሪካ የሚኖሩ ሰዎችን በኢትዮጵያ ጉዳይ ያላቸውን የተሳሳተ ምልከታ አስቀይረዋል:: ለዚህ ደግሞ ቤት ለቤት እየዞሩ ያስመረጧቸው ሰዎች አብነት ናቸው:: ለሰዎቹ እውነታውን በማስረዳትና በማሳየት አቋማቸውን እንዲቀይሩ አስችለዋቸዋል:: ወደመሀልም ያማጧቸው ሰዎች ጥቂት አይደሉም:: ከእነዚህ መካከልም ዶንባዬር የተባሉት ሰው በዋናነት ይጠቀሳሉ:: በአሜሪካ የሕዝብ ተወካይ ሲሆኑ፤ በውስጥ ሆነው በብዙ ነገር ደግፈዋቸዋል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ የመረጠውን መንግስት ማክበር ያስፈልጋል የሚለውን በማስረዳት እንዲሁም መሰረታዊ ስህተቶችን በማሳየት ጫና ከማድረግ እንዲቆጠቡም ሲያመላክቱ እነዚህንና መሰል ሰዎችን በመጠቀም መፍትሄ ተኮር ተግባራትን በማምጣት ነው::

‹‹የኢትዮጵያን እውነታን ማስረዳት ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአሜሪካም ጥቅም አለው›› የሚለው ዳንኤል፤ አንድ ዲሞክራቲክ ነኝ የሚል ሀገር በሌሎች ላይ ያላግባብ ጣልቃ መግባት ትክክል እንዳልሆነ ግልጽ ነው:: እውነታውን እየገለጡ መሄድ ሲገባም ተገቢ ባልሆነ መልኩ ጣልቃ መግባትም የነበረን መልካም ግንኙነት ያጠለሻል:: ስለሆነም ይህ እንዳይሆን በአብረን በኩል ነጻ ሀሳቦች፣ ዜና እና ወቅታዊ መረጃዎች ከእነ ዳራቸው በዌብሳይት በመልቀቅ የሚያቀራርብ ሥራ ተሰርቷል:: በዚህ ደግሞ አሜሪካዊያኑ ወደ እውነታው እንዲጠጉና ውሳኔዎቻቸውን እንዲቀይሩ እንዲሁም ጫናቸውን እንዲያቆሙ ማድረግ ተችሏል::

በአብረን ከሚዲያው ውጭም ሌሎች ተግባራት ተከናውነዋል:: ለምሳሌ፡- ፌስቲቫሎች ሲዘጋጁ ኢትዮጵያን የሚያስተዋውቁ ነገሮች እንዲካተቱ ማድረግ ላይ ይሰራል:: በተለይም ኢትዮጵያዊያን ይህንን ዝግጅት ካደረጉ ኢትዮጵያዊ መልክ ያለው እንዲሆን በተቻለው ሁሉ ሲደገፉ ቆይተዋል፤ አሁንም ይደገፋሉ:: በተጨማሪም የምርጫ ዘመቻ ሲደረግ ኢትዮጵያን እንዲቀላቀሉና መምረጥ በራሱ ብዙ ጥቅም አለውና ቤተእምነቶች ጭምር ድምጻቸው እንዲሰማ ለማድረግ ብዙ ጥረቶች ተደርገዋል::

አብረኖች በቋሚነት የሚሰሩት 15 አይሞሉም:: ያው በአጋርነት አብሯቸው የሚሰራው ብዙ ነው እንጂ:: እናም ቁጥራቸው አናሳ ቢሆንም ሀገራቸውን በእውቀት ከማገልገል ባሻገር በገንዘብም ደግፈዋል:: ለአብነት በጦርነቱ የተጎዱ ወገኖችን ለማገዝ ወደ ሁለት መቶ ሺህ የአሜሪካ ዶላር አበርክተዋል:: በተመሳሳይ ሕዳሴ ግድቡ ላይም እንዲሁ ሦስት ሺህ ዶላር በመስጠት የቻሉትን አድርገዋል:: አብረን እንደ ግል ማዋጣታቸው እንዳለ ሆኖ ከሌሎች ጋር መስራትን አቋማቸው አድርገው የሚንቀሳቀሱ ናቸው:: እናም በቀጣይም ሰዎች አንድ ላይ ተሰባስበው ትልቅ ሥራ መስራት ይኖርባቸዋል ብለው ስለሚያምኑ የሚያደርጉትን በጋራ እንዲጠራ ብቻ ነው የሚፈልጉት::

ዳንኤል እንደሚለው፤ ከብዙዎች ጋር ተቀራርቦ መስራት ምርጫው የሌለው ጉዳይ ነው:: ምክንያቱም ስኬትን ለማምጣት በየትም ይሁኑ ኢትዮጵያዊያን መተባበር አለባቸው:: ልማትን ከፍ ለማድረግ፤ ለተቸገሩ ለመድረስና የኢትዮጵያን አንድነት ለማረጋገጥ አብሮ መሆን የግድ ነው:: በአንድ ጉዳይ ላይ ተበታትኖ መስራት ደግሞ ውድቀት እንጂ እድገት አያመጣም:: እናም በአንድነት አብረን ለመሥራት እንነሳ ሲል ጥሪውን ያቀርባል::

**ልማትን ከፍ ለማድረግ፤ ለተቸገሩ ለመድረስና የኢትዮጵያን አንድነት ለማረጋገጥ አብሮ መሆን የግድ ነው:: በአንድ ጉዳይ ላይ ተበታትኖ መስራት ደግሞ ውድቀት እንጂ እድገት አያመጣም**

**የሕይወት ፍልስፍና**

ለአንተ እንዲሆንብህ የማትፈልገውን ነገር በሌላ ላይ አታድርግ:: ለአንተ ሊሆን የምትፈልገውን ለሌላም ተመኝ የሚለው ቃል የመጀመሪያው የሕይወት ፍልስፍናው ነው:: ሌላው ሕግ አክባሪ መሆን፤ አለማወቅን በማወቅ መቀየር መመሪያዎቹ ናቸው:: ምክንያቱም ባለማወቅ ውስጥ የሚመጣን ስህተት ማረም የሚቻለው በማወቅ ብቻ እንደሆነ ያምናል:: በተመሳሳይ ሰዎችን መረዳትና ማዳመጥ ከምንም በላይ አስፈላጊ ነው የሚል መርህ አለው::

**መልዕክት**

ለዲያስፖራው የሚኖረኝ መልእክት ብዙ ቢሆንም ጥቂቶቹን ላንሳ:: የመጀመሪያው ሀገር ወዳድነትን ለልጆቻችን እያስተማርን እናውርሳቸው የሚል ነው:: ማንነታቸውን፣ ባህላቸውንና ጀግንነታቸውን በመንገር እንዲሆኑት፣ እንዲኖሩት እናድርጋቸው:: ምክንያቱም መሰረቱ የጸና ልጅ መቼም ቢሆን የሚነቀንቁትና የሚጥሉት አይሆንም:: በሀገሩ ጉዳይም አይደራደርምም:: ለሀገሩ እድገትም የማይቆፍረው ድንጋይ አይኖርም:: አሁን ያለው ዲያስፖራ አይደለም ኢትዮጵያን ሌላ ሀገርን አቁሞ የሚያስቀጥል እንደሆነ ቢታመንም ልጆች ላይ ባለመሥራቱ ይህንን ማድረግ አልቻለም:: ስለዚህ ልጆች ላይ መሥራት ይታሰብበት ይላል::

ሌላው ያነሳው ነገር ደግሞ ለሁለቱም ሀገር ጠቃሚ መሆን ይቻላል የሚለው ነው:: ለአለንበት ሀገር ከማንም የማይተናነስና ተሰሚነት ያለው መሆን የመጀመሪያ ሥራችን መሆን ይገባዋል:: ከዚያ ሀገራችንን እንድትሰማ ማድረግ እንችላለን:: ምክንያቱም እዚያ ላይ ያሳረፍነው ጫና እኛን የሚያስከፋ አይሆንም:: በሌላ በኩል ደግሞ በልማት መሰማራት ነው:: እዚያ ሆኖ ገንዘብ በመላክ አለያም ቋሚ ሥራ በሀገር ውስጥ በመፍጠር ሀገርን ማገዝ ይቻላል:: ለዚህም አይሁዶች በማሳያነት ይነሳሉ:: ከአሜሪካ በአሉበት ደረጃ ማንም አያክላቸውም:: በተመሳሳይ ለእስራኤልም የማያደርጉት ነገር የለም:: ስለሆነም ከሌሎች ተምረን ሀገራችንን መገንባቱ ላይ መረባረብ ይኖርብናል መልእክቱ ነው::

ሀገራችን በምንም መልኩ እንድትጠቃና ጫና እንዲደረግባት በር መክፈት የለብንም ቀጣዩ ያደረገው መልዕክት ሲሆን፤ ውጭዎች ፖለቲካቸውን ከውጭ አይነዙም፤ ጭቅጭቃቸውም ቢሆን ከመድረኩ አይወጣም:: በአጠቃላይ ቆሻሻ ልብሳቸውን ውጭ አያሰጡም:: ንጹሁንና የታጠበውን ሀገራቸውን የሚገነባውን ነው ውጭ ላይ እንዲታይ የሚያደርጉት:: የዚህን ጊዜ ዓለም ማን እንደነሱ ይልላቸዋል:: እኛም ይህንን ነው ማድረግ ያለብን:: አንጣላም ማለት አይደለም:: እግርና እግርም ይጋጫል:: ስለዚህ ጸባችንን ጸሐይ አናሙቀው:: ሌሎች ሰምተው መዘባበቻ እንዲያደርጉን አንፍቀድላቸው:: እኛ የሚያምርብን ስንታረቅ፣ ችግራችንን በባህላዊ መንገዳችን ስንፈታ ነው:: ስለሆነም ያንን እያሰብን መንቀሳቀስ ይገባናል ሲል የመጨረሻ መልእክቱን ያስተላልፋል::

# "አዲስ አበባን ተመራጭ 'የማይስ' ቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ ይሰራል"

- አቶ ብዙዓለም ጌቱ

የቱሪዝም ሚኒስቴር የኮንቬንሽን ቢሮ የሽያጭ ዴስክ ማኔጀር

ዳግም ከበደ

**ኢትዮጵያ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫና የልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት ቢሮዎች ያሉባት ነች። ይህ አጋጣሚ ደግሞ ለማይስ ቱሪዝም ኢንዱስትሪ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። የማይስ ቱሪዝም ኢንዱስትሪ ዘርፉ በዋናነት የጉባኤ፣ የአውደ ርእይና ባዛር፣ የንግድ ውይይትና ዓለም አቀፍ ሁነቶችን ዋና ማጠንጠኛው በመሆኑ አገሪቱ ምጣኔ ሃብቷን እንድታሳድግ፣ ተመራጭ የስብሰባ ቱሪዝም ከተማ እንድትሆንና ያንን ተከትሎ ዜጎች በሚፈጠረው የሥራ እድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ልዩ እድል ይሰጣል።**

**መንግሥት ለቱሪዝም ዘርፉ የሰጠውን ልዩ ትኩረት ተከትሎም የማይስ ኢትዮጵያ የኮንቬንሽን ቢሮ ከሁለት አመት በፊት በይፋ ተመስርቷል። ይህ ቢሮም ኢትዮጵያን ከዓለም አቀፍ ጉባኤዎች እና ሁነቶች የቱሪዝም ተጠቃሚ የማድረግ ኃላፊነት ተጥሎበታል።**

**የዝግጅት ክፍላችን ባሳለፍነው ሳምንት የአፍሪካ ህብረት የመሪዎችና የሥራ አስፈፃሚ ጉባኤ በመዲናዋ አዲስ አበባ መካሄዱን ተከትሎ "የስብሰባ ቱሪዝምና የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታን" የሚያሳይ ዳሰሳ ማድረጉ ይታወሳል። በዛሬው እትማችን ደግሞ "የማይስ ቱሪዝምን የሚመራው የኮንቬንሽን ቢሮ ከተቋቋመ ወዲህ የተሰሩ ሥራዎችና የተገኙ ውጤቶች ምን ምን ናቸው?" በሚል በቱሪዝም ሚኒስቴር የማይስ ቱሪዝም የኮንቬንሽን ቢሮ የሽያጭ ዴስክ ማኔጀር ከሆኑት ከአቶ ብዙዓለም ጌቱ ጋር ያደረግነውን ቆይታ ይዘን ቀርበናል። መልካም ንባብ!!**



**አዲስ ዘመን፡- በቱሪዝም ሚኒስቴር ስር የኮንቬንሽን ቢሮ ከሁለት ዓመት በፊት ተቋቁሟል። ይህንን ቢሮ ለማዋቀር ያስፈለገበት ዓላማና ግብ ምን ነው?**

**አቶ ብዙዓለም፡-** የኢትዮጵያ ኮንቬንሽን ቢሮን ማቋቋም ያስፈለገበት ዋንኛ ምክንያት ኢትዮጵያ ከዓለም አቀፍ ስብሰባ፣ ኮንፍረንስ፣ ማበረታቻ ሁነቶች ተጠቃሚ እንድትሆን ታሳቢ በማድረግ ነው። አገሪቱ በዘርፉ ያላትን አቅም እንድትጠቀም እና የማይስ ቱሪዝም ፅንሰ ሃሳብን ለማስረፅ ቢሮው አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። ኢትዮጵያ የመጀመሪያውን የአፍሪካ ህብረት ጉባኤ ካስተናገደችበት ጊዜ አንስቶ ልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ መድረኮችን ስታዘጋጅ ቆይታለች። ሆኖም የስብሰባ ቱሪዝምን በተደራጀ መልኩ ማዋቀርና በትኩረት መስራት ስላልተቻለ ቀደም ሲል የተዘጋጁትም ሆኑ አዳዲስ ሁነቶች ወደ ሌሎች አገራት እንዲሄዱ ምክንያት ነበር። አሁን ይህንን ክፍተት ለመቅረፍ በማሰብ በተደራጀ መልኩ እየተሰራ ነው።

ቢሮው ኢትዮጵያ የንግድ ሁነቶች መዳረሻ እንድትሆን የልማት ስራዎችን በቀዳሚነት ሲሰራ ሌላው የኮንቬንሽን ማእከላትን በተመሳሳይ በማልማትና የገበያ ስራ በመስራት አገሪቱ በገቢ ተጠቃሚ እንድትሆን ይሰራል።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ በማይስ ቱሪዝም አቅም እንዳላት ለማሳየት በዓለም አቀፍ ደረጃ ምን እየሰራችሁ ነው?**

**አቶ ብዙዓለም፡-** ኢትዮጵያ የንግድ ሁነቶች ወይንም የኮንፍረንስ መዳረሻ መሆኗን በዓለም አቀፍ ደረጃ ሁነቶችን የሚገበዩ "International event buyers" የሚገኙባቸው ታላላቅ ኤግዚቢሽኖች፣ የንግድ ትርኢቶች (በስፔን ባርሴሎና የሚካሄደው አይ ቢቲ ኤም፤ በጀርመን ፍራንክፈርት አይ ኤም ኤክስ፤ በላስ ቬጋስ "ቬጋስ" የተሰኘ እንዲሁም በደቡብ አፍሪካ የሚደረጉ) የንግድ ሁነቶች አሉ። በእነዚህ መሰል ሁነቶች ላይ በመገኘት ኢትዮጵያ ያላትን የማይስ ቱሪዝም አቅምና ሁነት የማሰናዳት ብቃት ካስተዋወቅን በኋላ በተለያዩ የጨረታ ዘዴዎች በመግባት አሸንፈን ጥቅሙን ወደ አገራችን ለማምጣት አቅደን እየሰራን ነው። የኮንቬንሽን ቢሮው እየሰራ ያለውና ለመስራት ያሰበውም በዚህ መንገድ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ቢሮው ከተቋቋመ ጀምሮ እስካሁን የሰራችሁት ስራና ያስመዘገባችሁት ውጤት ምንድን ነው?**

**አቶ ብዙዓለም፡-** የኢትዮጵያ ኮንቬንሽን ቢሮ በይፋ የተመሰረተበት ጊዜ የኮቪድ ወረርሽኝ የተከሰተበት ወቅት ነበር። በዚህ ምክንያት ዓለም አቀፍ ሁነቶች በአዲስ እይታ እና አቅጣጫ እየተካሄዱ ነበር። በተለይ በዲጂታል ሚዲያ "virtual meeting" የሚካሄድበት ነበር። በዚህ ምክንያት በኢትዮጵያ ሊካሄዱ የነበሩ ብዙ ሁነቶችና ስብሰባዎች ተሰርዘዋል።

በዚህ ሂደት ውስጥ ግን ቢሮውን ማደራጀት፣ ብቁ ባለሙያ ማፍራትና በአፍሪካ ውስጥ ጥቂት የኮንቬንሽን ቢሮ ያላቸው አገራት ጋር ተወዳዳሪ መሆን የሚያስችል አቅም መገንባት ላይ ትኩረታችንን አድርገን ስንሰራ ቆይተናል። በተለይ ባለሙያዎችን ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በመተባበር የማሰልጠን ስራዎችን ሰርተናል። በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥም ለመስራት የቻልነው ሰራተኞችን ማብቃት ነው።

ኢትዮጵያ በዘርፉ ትልቅ አቅም እንዳላት ቢታወቅም በአዲስ አበባ ምን ያህል ብቁ ሆቴሎች እንዳሉና ሁነት ስብሰባዎችን ከማዘጋጀት አንፃር ያላቸውን አቅም የመለየት ስራን እያከናወንን ነው። ሌላው በክልል ከተሞች (በሁለተኛ ከተማነት) ብቁ የሆኑትን በተመሳሳይ እየለየን ነው። እስካሁን ድረስ "ለማይስ ቱሪዝም" ብቁ ናቸው ብለን ከለየናቸው ውስጥ ሀዋሳ፣ ቢሾፍቱ እንዲሁም ባህርዳር ይገኙበታል።

በተጨማሪ የኮቪድ ወረርሽኝ ስጋት መሆኑ ሲያበቃ በኢትዮጵያ ውስጥ ይካሄዱ ለነበሩ አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች ድጋፍ አድርገናል። በዓለም አቀፍ ደረጃ ድጋፍ ካደረግንላቸው ጉባኤዎች መካከል 17ተኛው የኢንተርኔት አስተዳደር ጉባኤ፣ ከሰሞኑ የተካሄደው የአፍሪካ ህብረትና የዓለም ሜትሮሎጂ ኮንፍረንስ ይገኙበታል። በአገር ውስጥም በተመሳሳይ የተካሄዱ ስብሰባዎችን እና መሰል የማይስ ዘርፎችን ደግፈናል።

**አዲስ ዘመን፡- ተግባራችሁን በምታከናውኑበት ወቅት ያጋጠማችሁ እክል አሊያም ፈተናዎች ምንድን ናቸው?**

**አቶ ብዙዓለም፡-** ቀደም ሲል ካነሳሁት የኮቪድ ወረርሽኝ ባሻገር በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የነበሩ ግጭቶች አዳዲስ ሁነቶችን በአገሪቱ ለማቀድና ለማምጣት ሁኔታዎችን ከባድ አድርገውት ነበር። በአንድ አገር ውስጥ ሰላማዊ ሁኔታ ከሌለ ይህን ማድረግ አስቸጋሪ ነው። በዚህ ምክንያት የተቀዛቀዘ ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር። ይሁን እንጂ ቀደም ብለው ማገገም የጀመሩት የቱሪዝም ዘርፉና የማይስ ንኡስ ዘርፍ ስለሆኑ ወደፊት ተስፋ ሰጪ ሁኔታዎች መኖራቸውን የሚያመላክት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ዓለም አቀፍ ሁነቶችን ወደ አገር ውስጥ ለማምጣት ከተቋሙ ጥረት ባሻገር እውቀቱና ልምዱ ካላቸው ግለሰብ ጎትጓቾች ጋር መስራትን ይጠይቃል። በዚህ ዙሪያ የእናንተ ልምድ ምን ይመስላል?**

> **በእነዚህ መሰል ሁነቶች ላይ በመገኘት ኢትዮጵያ ያላትን የማይስ ቱሪዝም አቅምና ሁነት የማሰናዳት ብቃት ካስተዋወቅን በኋላ በተለያዩ የጨረታ ዘዴዎች በመግባት አሸንፈን ጥቅሙን ወደ አገራችን ለማምጣት አቅደን እየሰራን ነው። የኮንቬንሽን ቢሮው እየሰራ ያለውና ለመስራት ያሰበውም በዚህ መንገድ ነው**

**አቶ ብዙዓለም፡-** የኢትዮጵያ ኮንቬንሽን ቢሮ እንደ ጎትጓች (lobbyist) ሆኖ ነው እየሰራ ያለው። የቱሪዝም ሚኒስትር ኮንቬንሽን ቢሮውን ቢያቋቁመም ሁነት አይደግስም። ነገር ግን ሁነቶችን ተጫርቶ ያመጣል። ከዚህ በተጨማሪ የዓለም አቀፍ ሙያ ማህበራት አባል የሆኑ ኢትዮጵያዊ ምሁራን እንዲሁም ኤክስፐርቶችን አምባሳደር በማድረግ ስብሰባዎች ሲኖሩ ወደ ኢትዮጵያ እንዲያመጡና ጨረታውን እንዲያግዙ ስትራቴጂ ቀርጸን፣ ሰነድ አዘጋጅተን ዝግጅታችንን ጨርሰናል።

**አዲስ ዘመን፡- ቀደም ሲል የማይስ ቱሪዝምን ለማዘጋጀት ብቁ ናቸው ያላችኋቸውን ሁለተኛ ከተሞች የመለየት ስራ እንደሰራችሁ አንስተህ ነበር። እነዚህ ከተሞች ተመራጭ ለመሆን ምን አይነት መስፈርት ማሟላት አለባቸው?**

**አቶ ብዙዓለም፡-** ሁለተኛ ከተማ ብለን የምንጠራቸው የማይስ መዳረሻዎች የተመረጡበት ምክንያት እና ከግምት ውስጥ የገባው መስፈርት በሆስፒታሊቲ ዘርፍ የሚያገለግሉ ሆቴሎች ያላቸው ጥራት፣ የአልጋ ብዛት፣ የጉባኤ ማከናወኛ አዳራሽና ማዕከላት ጥራትና ብዛት እንዲሁም ከቅድመ ሁነትና ድህረ ሁነት ዓለም አቀፍ ተሰብሳቢዎች ሊጎበኙዋቸው የሚችሏቸው የመስህብ ስፍራዎችና መዳረሻዎች መኖር አለመኖራቸው እንደ መስፈርት ተወስደዋል።

**አዲስ ዘመን፡- በቅርቡ 36ኛው የአፍሪካ ህብረት ጉባኤ በአዲስ አበባ ተካሂዷል። በዚህ ጉባኤ ላይ የኮንቬንሽን ቢሮው አገሪቱን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ምን ተግባራትን አከናወኗል? ምን ውጤትስ ተመዝግቧል?**

**አቶ ብዙዓለም፡-** እንደ ኮንቬንሽን ቢሮ ሳይሆን እንደ ቱሪዝም ሚኒስቴር ከህብረቱ ጉባኤ ኢትዮጵያን ተጠቃሚ ያደርጋሉ የተባሉ ሥራዎች ተከናውነዋል። ከዚህ ውስጥ ለተሰብሳቢዎቹ የኢትዮጵያን ቡና የማስተዋወቅ ሥራ ተሰርቷል። በአዲስ አበባ የሚገኙ አዳዲስ የመዳረሻ ስፍራዎችን ከማስተዋወቅ ባሻገር በጉባኤው ላይ የሚሳተፉ አንዳንድ አካላት ቆይታቸውን አራዝመው የመስህብ ቦታዎችን እንዲጎበኙ ለማስቻል መስሪያ ቤታችን በርካታ ሥራዎችን ሰርቷል። ይህ ጉባኤ በመሪዎች ደረጃ የሚካሄድ እንደመሆኑ በፈለግነው መንገድ ገብተን ያቀድናቸውን ሃሳቦች ማከናወን አስቸጋሪ ነው። ይሁን እንጂ በቀጣይ በሚካሄዱ መሰል ሁነቶች ላይ አዳዲስ ሃሳቦችን በማምጣት ለመስራት እናስባለን።

**አዲስ ዘመን፡- የአፍሪካ ህብረትን ጭምሮ ሌሎች ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች ሲኖሩ የጎንዮሽ ሁነት ማዘጋጀትና ከዚያም ተጨማሪ ጥቅም ማግኘትን በተመለከተስ?**

**አቶ ብዙዓለም፡-** ለዓለም አቀፍ ስብሰባ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡትን እንግዶች በአግባቡ ማስተናገድ ቅድሚያ ልንሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው። ትልቁ ነገር እንግዳ አቀባበልና መስተንግዶ ነው። ነገር ግን የጎንዮሽ ሁነቶችን ማዘጋጀት ላይ መሰራት እንዳለበትና ለዚያም መዘጋጀት እንደሚኖርብን እናምናለን።

**አዲስ ዘመን፡- በአጭርና በረጅም ጊዜ እቅድ ቢሮው ምን ለማሳካት አቅዶ እየሰራ እንደሆነ ቢነግሩን?**

**አቶ ብዙዓለም፡-** በአጭር ጊዜ መሰራት አለበት ብዬ የማምነው ዘርፉን ማጠናከር ላይ ነው። በአሁኑ ሰዓት እያከናወንናቸው ያሉ ዓለም አቀፍ ተሳትፎዎች አሉ። በእነዚህ ሁነቶች ላይ ቢሮው ብቻ ሳይሆን ሌሎች የግል አዘጋጆችንም አሳትፈን ይዘን እንሄዳለን። በልማት ሥራው ላይ ደግሞ አገር ውስጥ ያሉ ባለድርሻ አካላትን ማስተሳሰር ላይ ለመስራት አቅደን እየተንቀሳቀስን ነው። በተጨማሪ በግል ሁነት የሚያዘጋጁ አካላትን አቅም የመገንባት፣ አቅም ያላቸውን እውቅና ሰጥቶ ወደ ሥራ እንዲገቡ ማስቻል፣ ሆቴሎችን፣ የምግብና መጠጥ አገልግሎት የሚሰጡ የባህል አዳራሾች ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ የመደገፍ ስራዎችን እናከናውናለን።

በረጅም ጊዜ እቅድ ደግሞ አዲስ አበባን ተመራጭ "የማይስ" ቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ እንሰራለን። በአዲስ አበባ ትልልቅ የኮንፍረንስ ማእከላት አሉ። እነዚህን ማእከላት ለስብሰባ የሚያስፈልጉ ቴክኖሎጂዎችን ከመያዝ አንፃር አብዛኞቹ ክፍተት የሚታይባቸው ናቸው። ይህንን ክፍተት በመሙላት የተሻለ ስራ ለመስራት በቅንጅት ለመንቀሳቀስ እናስባለን። በተጨማሪ ትልልቅ የኮንቬንሽን፣ የስብሰባና የአውደ ርእይ ማእከላት ስለሚያስፈልጉ እነዚህ እንዲገነቡ የበኩላችንን እንሰራለን። የተጀመሩትም በቶሎ እንዲጠናቀቁ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት እንሰራለን።

# ሳምንቱን በታሪክ

# ጀግኖቹ

## ራስ ደስታ ዳምጠው፣ደጃዝማች በየነ መርዕድ እና ደጃዝማች ገብረማርያም ጋሪ

**ዋለልኝ አየለ**

ከዚህ በፊት በነበሩት ሳምንታት እንደገለጽነው ይህ የየካቲት ወር ታሪካዊ ክስተቶች የሚበዙበት ነው:: የካቲት 12 የሰማዕታት ጀግኖችን ተጋድሎ ዘክረናል:: በሚቀጥለው ሳምንት ደግሞ ኢትዮጵያን ስመ ገናና ያደረጋት የዓድዋ ድል አለ:: ይህ ሁሉ የሆነው በኢትዮጵያውያን ጀግኖች መስዋዕትነት ነው::

ከእነዚህ ጀግኖች ውስጥ፤ ከ86 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት የካቲት 13 እና 16 ቀን 1929 ዓ.ም በጀግንነት ጦር ሲመሩና ሲዋጉ በባንዳዎችና በግፈኛው የጣሊያን ወራሪ መስዋዕት የሆኑትን ራስ ደስታ ዳምጠው፣ ደጃዝማች በየነ መርዕድን እና ደጃዝማች ገብረማርያም ጋሪን እናስታውሳለን:: ደጃዝማች ገብረማርያም ጋሪ የካቲት 13 ቀን 1929 ዓ.ም የተሰው ሲሆን ራስ ደስታ ዳምጠውና ደጃዝማች በየነ መርዕድ ደግሞ የካቲት 16 ቀን 1929 ዓ.ም ተሰው:: በነገራችን ላይ ሁለቱ ጀግኖች(ራስ ደስታ ዳምጠው እና ደጃዝማች በየነ መርዕድ) የወቅቱን የኢትዮጵያ መሪ የቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴን ልጆች ነው ያገቡት::

ራስ ደስታ ዳምጠው የዓድዋው ሰማዕት የፊታውራሪ ዳምጠው ከተማ ልጅ ናቸው:: የተወለዱት ከዓድዋ ጦርነት ሁለት ዓመት በፊት በ1886 ዓ.ም ነው:: ከታላቅ ወንድማቸው ልጅ አበበ ዳምጠው (በኋላ ሌተናል ጀኔራል) ጋር የቤተ መንግሥት ባለሟል ሆነው ቆይተዋል::

ልጅ ደስታ ዳምጠው በ1916 ዓ.ም በፊታውራሪ ማዕረግ የፈረስ ዘበኛ (የፈረሰኞች ኃላፊ/አለቃ) ሆነው ተሾሙ:: ልጅ ደስታ ዳምጠው እየተባሉ ከልጅ ኢያሱ ወገኖች ጋር በሜኢሶ በተደረገው ጦርነት፤ ፊታውራሪ ደስታ እየተባሉም ራስ ጉግሳን ሊወጋ ወደ በጌምድር ከዘመተው የማዕከላዊ መንግሥት ጦር ጋር ተሰልፈው ተዋግተዋል::

ኅዳር 7 ቀን 1917 ዓ.ም የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን(አጼ ኃይለሥላሴ) ልጅ ልዕልት ተናኘወርቅን በተክሊል አገቡ:: በዚህም መስፍንናቸውንና ከንጉሳዊው ቤተሰብ ጋር ያላቸውን ዝምድና አጠናከሩ:: ይህ የተክሊል ጋብቻ ስነ ስርዓት ታኅሳስ 4 ቀን 1917 ዓ.ም በታተመው አዕምሮ ጋዜጣ ላይ ወጥቷል::


ራስ ደስታ በቅድሚያ በደጃዝማችነት ማዕረግ ከ1921 ዓ.ም ጀምሮ ከፋን ሲያስተዳድሩ ቆይተው በ1925 ዓ.ም «ራስ» ተብለው ሲዳሞንና ቦረናን እንዲያስተዳድሩ ተሾሙ። ፋሺስት ኢጣሊያ በ1928 ዓ.ም ኢትዮጵያን ስትወር ንጉሰ ነገሥት ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ የፋሽስትን ወረራ ለመመከት የክተት አዋጅ ካወጁ በኋላ የኢትዮጵያን ጦር በተለያዩ ግንባሮች እንዲመሩ ለጦር አበጋዞቻቸው ስምሪት ሰጡ::

በምስራቅ በኩል ወረራ የፈጸመውን ማርሻል ሩዶልፎ ግራዚያኒን ለመመከት ወደ ደቡብ ግንባር የዘመተው የኢትዮጵያ ጦር ቀኝ ደቡብ፣ መሐል ደቡብና ግራ ደቡብ በሚሉ ስያሜዎች በሶስት ምድቦች የተደራጀ ነበር። የቀኝ ደቡብ የጦር ሰራዊት ዋና አዛዥ የወቅቱ የሐረርጌ እንደራሴ የነበሩት ደጃዝማች ነሲቡ ዘአማኑኤል ነበሩ። የግራ ደቡብ ምድብ ዋና አዛዥ ደግሞ የወቅቱ የሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት ዋና ገዢ ራስ ደስታ ዳምጠው ሲሆኑ፤ የወቅቱ የባሌ ገዢ የነበሩት ደጃዝማች በየነ መርዕድ ደግሞ የመሐል ደቡብ ጦር ሰራዊት ዋና አዛዥ ነበሩ::

በሦስቱም ምድብ አዛዦች ስር ደግሞ ሌሎች የጦር አበጋዞች ሰራዊታቸውን ይዘው ተሰልፈው ነበር:: ከእነዚህም መካከል ደጃዝማች ሃብተሚካኤል ይናዱ፣ ደጃዝማች መኮንን እንዳልካቸው፣ ደጃዝማች አበበ ዳምጠው፣ ደጃዝማች አምደሚካኤል ሃብተሥላሴ እና ግራዝማች አፈወርቅ ወልደ ሰማዕት በደጃዝማች ነሲቡ ስር፤ ደጃዝማች ገብረማርያም ጋሪ፣ ደጃዝማች መኮንን ወሰኔ፣ ደጃዝማች ደባይ ወልደ አማኑኤልና ፊታውራሪ ታደሰ ገነሜ ደግሞ በራስ ደስታ ዳምጠው ስር፤ እንዲሁም በጅሮንድ ፍቅረስላሴ ከተማ፣ ፊታውራሪ አጥናፍሰገድ ወልደጊዮርጊስና ቀኛዝማች አስፋው ወልደጊዮርጊስ ደግሞ በመሐል ደቡብ ዋና አዛዡ በደጃዝማች በየነ መርዕድ ስር ተሰልፈው ነበር::


ራስ ደስታ ዳምጠው


ደጃዝማች በየነ መርዕድ


ደጃዝማች ገብረማርያም ጋሪ(አባ ንጠቅ)

ደጃዝማች ከበደ ተሰማ «የታሪክ ማስታወሻ» በሚለው መጽሐፋቸው ላይ ስለራስ ደስታ የጦር አሰላለፍና ፍፃሜያቸው እንዲህ ብለዋል::

« ... ደስታ ዳምጠው ራስ ከተባሉ በኋላም በፋሺስት ኢጣሊያ ወረራ ወቅት በሲዳሞ በኩል ከነበሩት የጦር አዝማቾች መካከል ዋነኛው ነበሩ:: ራስ ደስታ ዳምጠው በታክቲክ ለመዋጋት አስበው በመደራጀት ላይ ሳሉ በግንባር ቀድሞ እንዲዋጋ የታዘዘው ጦር አለቃ የነበረው ፊታውራሪ ታደመ አንበሴ ከድቶ ከፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ጋር ስለተሰለፈ ራስ ደስታ ችግር አጋጥሟቸው ነበር:: በተጨማሪም በደቡብ በኩል የነበረው የጠላት ወረራ የበረታ ስለነበርም ከንጉሰ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ጋር ሆነው ወደ ማይጨው እየዘመቱ የነበሩት ደጃዝማች ገብረማርያም ጋሪ ከሰሜን ተመልሰው ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመጓዝ ራስ ደስታን እንዲረዱና ጠላትን እንዲመክቱ ተደረገ::

አብዛኛው የሲዳሞ ጦር የደጃዝማች ባልቻ ሳፎ ነበር:: ደጃዝማች ባልቻ ከሲዳሞ ከተነሱ በኋላ ጦሩ በደጃዝማች ባልቻ ጊዜ የለመደው ግብርና ሽልማት ቀርቶበት ያኮረፈ ነበር:: አዲስ የተሾሙት የሲዳሞ አገረ ገዢም የራሳቸውን አሽከሮች በማደራጀት ልምድ ያለውን ይህን ጦር ፊት በመንሳት ስላደኸዩት በወቅቱ ወራሪውን ለመመከት ጥሪ ሲደረግለት ትዕዛዝ ለመፈፀም ሲል ብቻ ዘመተ እንጂ አገሬን፣ ጌታዬን ብሎ ተባብሮ በየጦር ግንባሩ ሊጋፈጥና ሊዋጋ አልፈቀደም ነበር ይባላል::

የአዲሱ አገረ ገዢ ባለሚሎችም የጦር ልምድ አልነበራቸውምና ምንም እንኳ ሰልፉና አደረጃጀቱ ቢያምርም በጦር ግንባር በሚገባ ሊዋጋና ሊመክት አልቻለም:: ራስ ደስታ ዳምጠው በዚህ ቅር ቢሰኙም ከደጃዝማች ገብረማርያም ጋር ከተገናኙ በኋላ ግን እስከመጨረሻው ድረስ በጀግንነት ተዋግተዋል:: ደጃዝማች ገብረማርያም የካቲት 13 ቀን 1929 ዓ.ም በውጊያ ላይ ሳሉ ሲሞቱ ራስ ደስታ በጠላት ተያዙ...» ብለዋል::

በሰሜንና በምስራቅ በኩል የማጥቃት ዘመቻ የከፈተው የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ዋና ከተማው አዲስ አበባ ድረስ ዘልቆ መግባት ቢችልም በደቡብ በኩል የነበረው ጦር ግን ከነራስ ደስታ ዳምጠው እና ከነደጃዝማች ገብረማርያም ጋሪ በኩል በገጠመው የመከላከልና የማጥቃት ዘመቻ ምክንያት ወደ አዲስ አበባ መድረስ ስላልቻለ የግንባሩ ጦር አዛዥ ጀኔራል ጀሎዞ እና ዋናው የአስተዳደሩ ተወካይ ማርሻል ሩዶልፎ ግራዚያኒ ለራስ ደስታና ለደጃዝማች ገብረማርያም ልመና፣ ማስፈራሪያና ማስጠንቀቂያ የተቀላቀሉባቸው ደብዳቤዎችን ጽፈውላቸው ነበር::

ጥር 1 ቀን 1929 ዓ.ም ሻንቆ በተባለው ቦታ ላይ በተደረገው ውጊያ ኢትዮጵያውያን በጠላት እግረኛ ጦር ላይ ከፍተኛ ድል ቢቀዳጁም የጠላት ጦር በአውሮፕላን የሚያዘንበውን ቦምብና መርዝ ግን መቋቋም አልተቻለም:: በመሆኑም አርቤጎናን በመልቀቅ ብዙ የወገን ጦር ወዳለበት ወደ ባሌ ግዛት ለመሄድ ተወሰነ:: ውጊያው በመንገድ ላይም አላባራም ነበር:: የወገን ጦር መንገድ የዘጋበትን የፋሺስት ጦር በመውጋት መንገድ እያስከፈተ ዘለቀ::

ጥር 20 ቀን 1929 ዓ.ም ራስ ደስታ ዳምጠው፣ ደጃዝማች ገብረማርያም ጋሪ፣ ደጃዝማች በየነ መርዕድ፣ ደጃዝማች በዛብህ ስለሺ እና ፊታውራሪ ሽመልስ ሀብቴ ጦራቸውን ይዘው እነርሱም መድፍ ጠምደው ተሰለፉ:: በዚህ ተጋድሎ ኢትዮጵያውያን አካባቢው በጠላት እጅ እንዳይወድቅ ከማድረጋቸውም ባሻገር በጠላት ጦር ላይ ትልቅ ጉዳት ማድረስ ችለዋል::

ደራሲና ጋዜጠኛ ጳውሎስ ኞኞ «የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት» በሚለው መጽሐፉ እነራስ ደስታ ዳምጠው ከፋሺስት ጦር ጋር ስላደረጉት ፍልሚያ በጻፈበት ክፍል « ... በኢትዮጳያውያን በኩል በራስ ደስታ ዳምጠው አዝማችነት 40 ሺህ የሲዳሞና የባሌ ጦር፣ በደጃዝማች ነሲቡ ዘአማኑኤል አዝማችነት 30 ሺህ የኦጋዴንና የሐረርጌ ጦር፣ በደጃዝማች አምደ ሚካኤል አዝማችነት 10 ሺህ የአርሲ ጦር በየቦታው በደቡብ አቅጣጫ ተሰልፎ ነበር:: በቤኒቶ ሙሶሊኒ ትዕዛዝ የሰሜኑ ጦር የመረብን ወንዝ ሲያቋርጥ የሩዶልፎ ግረዚያኒ ጦርም በዚያው ድንበር አልፎ ኦጋዴን ገባ:: በሦስት ሳምንታት ጊዜ ውስጥም ቀላፎ፣ ገርለ ጉቢና ቆራሄ በፋሺስት ኢጣሊያ ወታደሮች ተያዙ:: በኢትዮያውያን በኩል የራስ ደስታ ጦር ከነገሌ ጀምሮ ዶሎ ድረስ ያለውን ቦታ እንዲጠብቅ ስለታዘዘ 400 ኪሎ ሜትር ያህል በእግሩ ተጉዞ በወሰን አካባቢ እንዲደርስ ተደረገ:: ጦሩ በሚጓዝበት ጊዜ ለአውሮፕላን ጥቃት አመቺ ሆኖ በመገኘቱ በፋሺስት የጦር አውሮፕላን ቦምብ እየተደበደበ ነበር:: ከሞት የተረፈውም ከኢትዮጵያና ሶማሊያ ድንበር ደርሶ ተሰለፈ ...

... ይህን የኢትዮጵያን መንቀሳቀስ ያጠናው ማርሻል ባዶሊዮ በቴሌግራም ቁጥር 1897 ለግራዚያኒ መልዕክት አስተላለፈ:: መልዕክቱም ‹የኢትዮጵያ ጦር ሰራዊት ዋና ኃይል ወደ እናንተ መጓዝ ጀምሯልና በእጅህ በሚገኘው ማንኛውም ዓይነት መሳሪያ በቦምብና በመርዝ ሁሉ መዋጋት አለብህ:: ከዚህ ኃይል በኋላ ሌላ የሚያጠቃህ ያለ አይመስለኝም:: እርግጠኛ ነኝና እንደእኔ ከሆነ ብታስብበት የሚከፋ አይመስለኝም› የሚል ነበር::

በኅዳር ወር ግራዚያኒ ዶሎ ገብቶ ጦሩን ሲያጠናክር ከርሞ ዝግጅቱን ከጨረሰ በኋላ ወደፊት በመግፋት ጥር 4 ቀን 1928 ዓ.ም የመጀመሪያው ታላቅ ውጊያ ገናሌ፣ ዶሪያ ላይ ተካሄደ:: በዚያም ቀን በኢትዮጵያ ሰራዊት ላይ በምድር በታንክና በዘመናዊ መሳሪያ የሚደረገው ውጊያ አንሶ በአውሮፕላን አንድ ሺህ 700 ኪሎ ግራም የሚመዝን ቦምብና የመርዝ ጋዝ ተጣለበት::

የኢጣሊያ ጦር የጎድጓድ ውሃና ወንዝ ካለበት ቦታ እየመሸገ ስለተቀመጠ የኢትዮጵያን ሰራዊት ውሃ እንዳያገኝ አደረገው:: የኢትዮጵያ ሰራዊት ከወንዝም ሆነ ከጉድጓድ ውሃ ለመቅዳትና ለመጠጣት ሲጠጋ በየአካባቢው የመሸገው የኢጣሊያ ጦር በመትረየስ ይገድለዋል:: ግድያው ሰውን በመምረጥ ብቻ ሳይወሰን እንስሳትም ውሃ ሲጠጡ ይገደሉ ነበር:: ከላይ ከአየር ደግሞ አውሮፕላኖች በመመላለስ በመርዝ ጭስ ፈጁት ... »

በነራስ ደስታ ዳምጠው ይመራ የነበረው የኢትዮጵያ ሰራዊት በእግረኛ ጦር ውጊያ ድሎችን ቢያስመዘግብም የፋሺስት ኢጣሊያ የጦር አውሮፕላኖች የሚያዘንቡበትን ቦምብና የመርዝ ጭስ መቋቋም እጅግ አስቸጋሪ ስለሆነበት አካባቢው በጠላት ጦር ቁጥጥር ስር ዋለ:: ራስ ደስታ ዳምጠውም በባንዳዎችና በፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ትብብር ተማርከው የካቲት 16 ቀን 1929 ዓ.ም ተገደሉ:: የፋሺስት ጦር ከኢትዮጵያ ከተባረረ በኋላ አፅማቸው በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በክብር እንዲያርፍ ተደርጓል። አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኘው «ራስ ደስታ ዳምጠው ሆስፒታል» ለእርሳቸው መታሰቢያ የተሰየመ ነው።

ራስ ደስታ ከአርበኝነታቸው በተጨማሪ፣ የአውሮፓንና የአሜሪካን ዘመናዊነት ወደ ኢትዮጵያ ለማምጣት መንገድ፣ የንፁህ ውሃ አገልግሎት፣ የህክምና፣ የትምህርት ወዘተ... ተቋማትን ለማስፋፋት የበኩላቸውን ቅስቀሳ ያደርጉ ነበር። የነጮችን ዘመናዊነት ለመቅሰም ፍላጎት ቢኖራቸውም «ነጮችን አያምኑም» ይባል ነበር። ራስ ደስታ በ1923 ዓ.ም ወደ አሜሪካ ተጉዘው እንደነበርና ከወቅቱ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ፍራንክሊን ዴላኖ ሩዝቬልት ጋር ተገናኝተው እንደተመለሱም ታሪካቸው ያሳያል።

ደጃዝማች በየነ መርዕድ በሰሜን ሸዋ 1889 ዓ.ም እንደተወለዱ ይነገራል:: ደጃዝማች በየነ መርዕድ የቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴን ልጅ ልዕልት ሮማነወርቅ አግብተዋል::

ደጃዝማች በየነ በፋሽስት ጣሊያን ወረራ ወቅት በርካታ የጦር ተጋድሎዎችን አድርገው ለአገራቸው ተሰውተዋል::

ደጃዝማች ገብረማርያም ጋሪ(አባ ንጠቅ) በ1866 ዓ.ም ምዕራብ ሸዋ፣ አገምጃ ውስጥ ልዩ ስሙ ሰርቦኦዳ ኮሎ በተባለ ቦታ ከአባታቸው አቶ ጋሪ ጎዳና እና ከእናታቸው ወይዘሮ ሌሎ ጉቴ 13ኛ ልጅ ሆነው ተወለዱ::

ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ስትወር የ22 ዓመት ወጣት የነበሩት ገብረማርያም ጋሪ ለንጉሰ ነገሥቱ የክተት አዋጅ ምላሽ በመስጠት ከበጅሮንድ ባልቻ ሰራዊት ጋር ዘመቱ:: የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም ጦርነቱ ሲጀመር ጎህ ሲቀድ ወደ ውጊያ የገባው የበጅሮንድ ባልቻ ጦር እጅግ ከባድ ውጊያ አደረገ:: ገብረማርያም አዝማቻቸው በጅሮንድ ባልቻ ጭምር እንዲቆስሉ ምክንያት ከሆነው ጦርነት ተርፈው የድሉ ተቋዳሽ መሆን ቻሉ:: እኚህ ለአገራቸው በክብር ለመሰዋት የተፈጠሩ ጀግና ከ40 ዓመት በኋላ በመጣው የፋሽስት ጣሊያን ወረራ ወቅት ግን በ63 ዓመታቸው መስዋዕት ሆኑ::

አዲስ አበባ ከተማ የሚገኘው «ሊሴ ገብረማርያም ትምህርት ቤት በስማቸው ተሰይሞላቸዋል::

# የዝነኞች ገጽ

## ታላቁ ብስክሌተኛ- ገረመው ደንቦባ

**ዳግም ከበደ**

አንጋፋ ስፖርተኛ ናቸው። ለተሳተፉበት የስፖርት ዘርፍ በኢትዮጵያ እንዲሁም በዓለም ኦሊምፒክ ፈር ቀዳጅ ናቸው። ይሄ ግነት ሳይሆን ታሪክ ቁልጭ አድርጎ በገፆቹ የከተበው እውነት ነው። እኚህ ሰው ለአገር ባለውለታ ናቸው። ስፖርቱ አሁን ካለበት አንፃር ከተመለከትነው የእርሳቸው ሚና የእውነትም ገኖ ሊታየን ይችላል። ለመሆኑ እኚህ ስፖርተኛ ማን ናቸው? በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ የብስክሌት ስፖርት ተወዳዳሪ፣ የኦሊምፒክ ተሳትፎ ፈር ቀዳጅ፣ አሰልጣኝ እንዲሁም የጠንካራ ስብእና ባለቤት ጋሽ ገረመው ደንቦባ።



በኢትዮጵያ የብስክሌት ስፖርት እንዲሁም የኦሊምፒክ ተሳትፎ ታሪክ ደማቅ አሻራቸውን ካሳረፉ ድንቅና ግንባር ቀደም ስፖርተኞች አንዱ የሆኑት ብስክሌተኛ ገረመው ደንቦባ በሕክምና ሲረዱ ቆይተው ከቀናት በፊት በ90 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡ ስርአተ ቀብራቸውም ከትናንት በስቲያ በብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተ-ክርስቲያን ተፈፅሟል፡፡

አዲስ ዘመን በአንድ ወቅት ከእኚህ ታላቅ የስፖርት ሰው ተነግሮ የማያልቅ ስፖርቱ ዓለም ትዝታ፤ የሕይወት ጉዟቸውን እንዴት እንዳሰመሩት እንዲሁም ለሚወዱት ስፖርት እድገት ያላቸውን ልምድ ለትውልድ እንዲያጋሩ ሰፋ ያለ ቃለ መጠይቅ አድርጎላቸው ነበር። በዚህ ቃለምልልስ ወቅት ጠንካራው ሰው ህመም አሸንፏቸው ከቤት ውለዋል። በህክምና ላይ እንደነበሩ ለመረዳትም አያዳግትም። በአፍንጫቸው ላይ ኦክስጂን ሰክተዋል። እግራቸው ላይ ያጋጠማቸው ጉዳት ብዙም አያራምዳቸውም። እንደዚያም ሆኖ ግን እኛን በእንግድነት መቀበል አላቃታቸውም። እንዳደጉበት ባህል ኖር አሉን። ለጥያቄያችንም ሳይሰስቱ ከታሪክ ባህራቸው እየጨለፉ አጫወቱን። ብዙ የመውጣት እና የመውረድ የሕይወት ሂደቶች ላይ ያወጉንን ጨምረን ረጅሙን የስፖርት ታሪካቸውን ከብዙ በጥቂቱ እንዳስሳለን።

ጋሽ ገረመው በእርሳቸው ዘመን ባላቸው ጥንካሬ ለአገር በብስክሌት ስፖርት ፈር ቀዳጅ ውጤቶችን አስመዝግበዋል። እነ አበበ ቢቂላን፣ ማሞ ወልዴ፣ ይድነቃቸው ተሰማ ለዚህች አገር ከሰሩት ውለታ በማይተናነስ በብስክሌት ስፖርት ላይ ተጠቃሽ ስራን የሰሩ ታላቅ ባለውለታ ናቸው። ለዚህ ደግሞ የታሪክ ዶሴዎችን በቀላሉ መግለጥ በቂ ነው።

### ዘመነ ጣሊያን ወረራ እና የጋሽ ገረመው

የጋሽ ገረመው የትውልድ ከተማ አዲስ አበባ ነው። አንዋር መስጊድ ፊት ለፊት ሀብተ ጊዮርጊስ ድልድይ እየተባለ በሚጠራው ሰፈር ነው ተወልደው ያደጉት። ጣሊያን አይኑን በጨው አጥቦ ኢትዮጵያን በድጋሚ ለመውረር ሲገባ የያኔው እምቦቃቅላ ኋላም አንጋፋ ስፖርተኛ ጋሽ ገረመው ከተወለዱ የአንድ አመት እድሜ አስቆጥረው ነበር። በወቅቱ ለኢትዮጲያውያን መርገምትን ይዞ ከተፍ ያለው ፋሽስት ጣሊያን ግን ለርሳቸው የወደፊት ህልም ፈር የቀደደ አጋጣሚን ፈጥሮ ነበር። መቼም ሁሉም ነገር መጥፎ አይሆንም። ወራሪ ወታደሮቹ ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ የጣሊያን ስሪት የሆኑትን እነ ቢያንኪ፣ባርታሊ እንዲሁም ቦንሲት የሚል ስያሜ ያላቸው ብስክሌቶችን ይዘው ገብተው ነበር። ታዲያ እነዚህ ብስክሌቶች ፋሽስት በጀግኖች አርበኞች ድል ተደርገው ከኢትዮጲያ ጨርቃቸውን ጥለው ሲወጡ በምርኮነት አገር ውስጥ ቀርተው ነበር።

ፋሽስት በአምስት ዓመት የቆይታ ጊዜው ወታደሮቹ በአዲስ አበባ ብስክሌቶችን በጎዳናዎች ላይ በመንዳት፣ ሰዎችን በማለማመድ እና ውድድር በማካሄድ የኢትዮጵያውያንን ልብ ለመማረክ ጥረት ያደርግ ነበር። በወቅቱ በዓለም ላይ በተለይ በፈረንሳይ፣ ቤልጂየም እንዲሁም ሆላንድ የመሳሰሉ አገራት ብስክሌት ተወዳጅ እና ቀዳሚው ስፖርት ነበር። ለዚህ ስፖርት ኢትዮጲያውያኑ እንግዳ ቢሆኑም በቀላሉ እውቀቱን በመቅሰም ጥሩ ችሎታን አዳብረው ነበር። በጎዳናዎች ላይ አንደ ድንገት ከወራሪዎቹ ጣሊያኖች ጋር ሲገናኙ እንኳን በቀላሉ እያለፏቸው ይጓዙ ነበር። በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለ ፋሽስት ከአገሪቷ ሳይወድ በግዱ ተባረረ። የብስክሌት ስፖርት ግን በኢትዮጲያ ተወዳጅነቱ ቀጠለ። ድሮውንም ኢትዮጵያውያን ከፋሽስት እንጂ ከስፖርቱ ቂም አልነበራቸውም። የወደፊቱ ባለታሪክ ጋሽ ገረመውም ጣሊያን ሲወጣ ስድስት አመት ሞላቸው። እድሜያቸው ለአስኳላ ደርሶ ዘመናዊውን ትምህርት ተያይዘውት ነበር።

### የጋሽ ገረመው የብስክሌት ወዳጅነት ጅማሮ

የጋሽ ገረመው ብስክሌትን የተዋወቁት ገና በጨቅላ እድሜያቸው ውድድሮችን በመመልከት ነው። በአምስት እና ስድስት አመታቸው እነ ካሳ ፈዲር፣ ኤርትራዊው ካሳ ርእሶም፣ ሙሉጌታ ካሳ፣ታዬ ክፍሌ የሚባሉ ብስክሌተኞች ከአንዋር መስጊድ ፊት ለፊት እነኡስማን ኪኪያ ሱቆች አካባቢ እነ እራስ ሃይሉን የመሳሰሉ ታላላቅ መሳፍንት እና መኳንንቶች በክብር ቦታቸው ላይ ተቀምጠው ውድድር ሲያደርጉ ሲመለከቱ ጋሽ ገረመውም በራፋቸው ላይ ሆነው በደረታቸው ተኝተው ይከታተሉ ነበር። ከስፖርቱ ጋር ወዳጅነት የጀመሩትም በዚያን ወቅት ነበር።

ጋሽ ገረመው በአንዋር መስጊድ ቢያጆ ተራ ብስክሌት እያከራዩ የሚያለማምዱ ልጆች ጋር በሰባት ዓመታቸው ግንኙነት ጀመሩ። አምስት እና አስር ሳንቲም ከቤተሰቦቻቸው እየወሰዱ በመክፈል ልምምዳቸውን አጧጧፉት። ቁመታቸው ገና ቢሆንም እግራቸውን በፔዳሉ መካከል እያሾለኩ ቆመው በመንዳት ተለማመዱ። በዘጠኝ ዓመታቸው ግን የብስክሌቱ ኮርቻ ላይ መቀመጥ ቻሉ። እድሜያቸው እየጨመረ ሲሄድ ግን ከብስክሌቱ ጋር ግንኙነታቸው እየጠነከረ መጣ። ጋሽ ገረመው ለቤተሰቦቻቸው አስራ አንደኛ ልጅ ናቸው። ሆኖም እናታቸው ወይዘሮ ቶላ ኢጀሬ ለእርሳቸው የተለየ ፍቅር ነበራቸው። በኮከበ ፅባሕ ትምህርት ቤት በእግራቸው እየተመላለሱ ይማሩ ስለነበርም ለልጃቸው ብስክሌት በ30 ብር ገዝተው ለመስጠት አላመነቱም ነበር። የግል ብስክሌት ገና በልጅነታቸው በእጃቸው በማስገባት ከቤት ወደ ትምህርት ቤት፣ ከትምህት ቤት ወደ ቤት ጓደኞቻቸውን እያፈናጠጡ ( ከኋላ እየጫኑ) ይመላለሱ ጀመር። ይሄ ደግሞ የብስከሌት የመንዳት ብቃታቸውን እና ጥንካሬያቸውን እየጨመረው መጣ።

ጊዜው 1943 ዓ.ም ነው። በአካባቢያቸው የታዳጊዎች እና ወጣቶች የብስክሌት ውድድሮች ይካሄዱ ነበር። ታዲያ የያኔው ታዳጊ ጋሽ ገረመው በዚህ ውድድር ላይ በመሳተፍ ድል ማድረግን አሀዱ አሉ። ለተራ የትራንስፖርት አገልግሎት በሚጠቀሙባት ብስክሌት ጓደኞቻቸውን ከኋላ አስከትለው ውድድሩን ሰባተኛ ደረጃ በመያዝ አጠናቀቁ።

70 የሚደርሱ ተወዳዳሪዎች ተሳታፊ ነበሩ። በጊዜው ለእርሳቸው ጥሩ ውጤት ቢሆንም እንዴት አንደኛ መውጣት አልችልም የሚል ቁጭት ውስጥ ግን ከቷቸው ነበር። ጓደኞቻቸውን እያፈናጠጡ የጀመሩት የብስክሌት ስፖርት በውድድሮችም እየተገነባ ከጊዜ ወደ ጊዜ



የስፖርት ተክለ ሰውነታቸው እና ጡንቻቸው እየፈረጠመ መጣ። ከተራ ፍቅር ቅልጥ ወዳለው የብስክሌት ሱስ ውስጥ ተንደርድረው ገቡ።

### ጋሽ ገረመው በታላቁ የኦሊምፒክ መድረክ

ታላቁ ብስክሌተኛ ጋሽ ገረመው በኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ታሪክ በመጀመሪያ ተሳትፎ በሆነው እኤአ 1956 የሜልቦርን ኦሊምፒክ ከመሳተፋቸው በፊት ብዙ ውጣ ውረዶችን አሳልፈዋል። ኦሊምፒኩን ወዳዘጋጀችው አውስትራሊያ ጋሽ ገረመውና የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ቡድን ያደረገው የጉዞ ውጣ ውረድ በራሱ አንድ መጻሐፍ ይወጣዋል።

ለንጉሰ ነገስት ቀዳማዊ ኃይለስላሴ በሜልቦርን በኦሊምፒክ ኢትዮጵያ ወደ ውድድር ከፍታ እንድትመጣ ጥያቄ ያቀረቡት ገረመው ደንቦባ ነበሩ። በወቅቱ ታታሪው ወጣት ወደ ቢሾፍቱ ለልምምድ የሚወጡበት እሁድ ቀን ነው። ኦሊምፒያን ገረመው ደንቦባ ሁሌም በዚህ ቀን 42 ኪሎ ሜትሮችን በቢያንኪ ብስክሌታቸውን ይጋልባሉ።

የወጣት ፍላጎታቸው እና አገርን የማስጠራት አላማቸው ገንፍሎ ወጥቶ "ለምን በዓለም አልሳተፍም" የሚል ጥያቄ በውስጣቸው ይመላለስ ነበር። ግን ይህን ብቻቸውን ማድረግ እንደማይችሉ ያውቁታል። ምክንያቱም ኢትዮጵያ በወቅቱ የዓለም ኦሊምፒክ ኮሚቴ የሚባል አልነበረችም። ወቅቱም ገና 1946 ዓ.ም ነው። የስፖርት ተቋማት አልተገነቡም። በመንግስት ተቋማት ላይ ተፅእኖ አልፈጠሩም። ስለዚህ ተናጥላዊ ጥያቄ እንጂ ከተቋም የሚመጣ የእንሳተፍ አላማ የለም።

ይህንን የእንሳተፍ ጥያቄ ኦሊምፒያን ገረመው ደንቦባ አነሱት። ንጉሰ ነገስቱን ቢሾፍቱ መስመር ላይ አገኟቸው።

"የእሳቸው መኪና እንደሆነ ገብቶኛል። የተረዳሁት እሱን ነው። ይህንን አጋጣሚ ደግሜ እንደማላገኘው አውቃለሁ። ስለዚህ መጠቀም አለብኝ። በቀኝ እጄ ብስክሌቱን ይዤ፣ ግራ እጄን ወደላይ ከፍ አድርጌ አወጣሁት። ንጉሱ ይህንን ያዩ ኖሯል። ትንሽ ጠበቁኝ እና መኪናቸውን አቁመው ምን እንደምፈልግ ለሾፌሩ ሙሴ ነሲብ ጠየቁት" በማለት ያንን ጊዜ ያስታውሱታል።

ከዚህ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ከንጉሱ እንዲህ የሚል ጥሪ ደረሳቸው "የሚመጣው ሳምንት ገነተ ልዑል ቤተመንግስት እንድትገኝ"። ብስክሌተኛው ጊዜ አላባከኑም ለንጉሱ ጥሪ እጅ ነስተው ስራቸውን ቀጠሉ።

ታሪክ አዋቂው ገረመው ደንቦባ በቀጠሮው ቀን ተገኙ። ንጉሱ የየሳምንት ችሎት፣ ጥያቄዎች የሚመለሱበት አዳራሽ ውስጥ ሲገቡ ሁሉም የክብር ሰላምታ ሰጧቸው ካባቸውን ነስንሰው ተቀመጡ።

ያንን አጋጣሚም ሲያስታውሱ "የእኔ ጥያቄ ከትንሽ ቆይታ በኋላ አዳራሹ ውስጥ ተነበበ። ፍላጎቴ ኢትዮጵያ በዓለም (ኦሊምፒክ) እንድትሳተፍ ነው። ይህንን ተሳተፉ የሚለውን ምላሽ ነው የምጠብቀው። ተነቦ ካለቀ በኋላ ጥያቄውን ንጉሱ እንደተቀበሉት ተናገሩ። የተሰማኝ ደስታ በልጅነቴ ኤሌክትሪክ ሲይዘኝ የነዘረኝን አስታወሰኝ። እንደዛን ቀን ደስተኛ ሆኜ አላውቅም። በጉልበቴ ተንበርክኬ አመስግኜ ከአዳራሹ ወጣሁ" በማለት በአንድ ወቅት ተናግረዋል።

ከዚህ በኋላ ብስክሌተኛ ገረመው ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በተሳተፈችበት የሜልቦርን ኦሊምፒክ በብስክሌት ስፖርት ኢትዮጵያ ወክለው በመሳተፍ እና ሰንደቅ አላማዋን በመያዝ ቀዳሚው አትሌት ለመሆን አውስትራሊያ ሜልቦርን ተገኙ። በሜልቦርን ኦሊምፒክ ተሳትፏቸውም ኢትዮጵያ ከዓለም ዘጠነኛ ደረጃን ይዛ እንድታጠናቅቅ ታላቅ የጀግንነት ፍልሚያ አድርገዋል። ይህም ውጤታቸው በታሪክ በስፖርቱ ትልቅ ውጤት ሆኖ ይጠቀሳል።

ቀጣዩ የ1960 የሮም ኦሊምፒክም ታሪክ ነው። በዚህ ኦሊምፒክ ጠንካራው ኢትዮጵያዊ የብስክሌት ተወዳዳሪ ከውድድሩ አስቀድሞ ትልቅ የአሸናፊነት ግምት የተሰጣቸው ሰው ነበሩ። ለዚህ ደግሞ አቅሙም እድሉም ነበራቸው። ግን ቀዳሚ የማሸነፍ እድል የተሰጣቸው ኢትዮጵያዊ ውድድር ላይ እያሉ ያልተጠበቀ አደጋ አጋጠማቸው። ከ11 ዙር ውስጥ 9ኙን በአንደኝነት እየመሩ ያሸንፋሉ ተብሎ ሲጠበቅ በድንገት ከኋላ ተገጭተው በመውደቃቸው ውድድሩን አቋርጠው ለመውጣት ተገደዱ። ይህም በወቅቱ አንጋፋው ብስክሌተኛ ገረመው ተገቢ ያልሆነ ግጭት ባያስተናግዱ ማሸነፍ ይችሉ እንደነበር በዓለም ጋዜጦች ጭምር ተዘግቦላቸዋል። በዚህም ለ9 ዙር የሮሙን የብስክሌት ውድድር በመምራት ሰፊ ሙገሳ እና ክብርን በማግኘት ታሪክ ይዘክራቸዋል። በዚያ ኦሊምፒክ ጋሽ ገረመው በድንገተኛው አጋጣሚ ከውደድሩ በጉዳት ቢወጡም፤ አበበ ቢቂላ በባዶ እግሩ ሮምን ወሮ የጓደኛውን ሀዘን በደስታ አካካሰው።

ገረመው ደንቦባ በቀጣዩ 1964 የቶኪዮ ኦሊምፒክም በዋና አሰልጣኝነት የኢትዮጵያን የብስክሌት ቡድን መምራት የቻሉ ሲሆን፣ በተወዳዳሪነት ዘመናቸው በተለያዩ ዓለም አቀፍ መድረኮች ከ30 በላይ ዋንጫ እና 32 የወርቅ ሜዳሊያዎች ማስመዝገብ እንደቻሉ ከሕይወት ታሪካቸው ማህደሮች መረዳት ይቻላል።

ጋሽ ገረመው በኢትዮጵያ ብስክሌት ስፖርት ታሪክ ውስጥ የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳሉ። በቶኪዮ ኦሎምፒክ ላይም የብስክሌቱን ልኡካን ቡድን በአሰልጣኝነት በመምራት አገልግለዋል። ከዚያም በኋላ ለረጅም ዓመታት በአሰልጣኝነት ለአገር ውለታ ሰርተዋል። በምላሹ ግን ለአገራቸው ክብር እግራቸው ተሰብሮ ብረት ሲያጠልቁ «አባ ከና» ያላቸው የለም።

ገረመው ደንቦባ በኢትዮጵያ ብስክሌት ስፖርት ታሪክ ውስጥ ትልቅ አሻራን ከማሳረፋቸው ባሻገር አቅማቸው ደክሞ እቤት መዋል እስከጀመሩበት ቅርብ ጊዜ ድረስ በተለያዩ መድረኮች እየተገኙ ልምዳቸውን በማካፈል ይታወቃሉ። ከእሳቸው በኋላ በኢትዮጵያ ብስክሌት ስፖርት ታሪክ ጎልተው መውጣት ለቻሉት እንደ ለተሰማ አሞሳ፣ አድማሱ መርጋ፣ አላዛር ክፍሎም፣ ጆቫኒ ማሶላ፣ ጀማል ሮጎራና ጽጋቡ ገብረማርያም ለመሳሰሉ ብስክሌተኞች አርአያ መሆን ችለዋል።

# ዓለም አቀፍ



## ከማሊና ቡርኪና ፋሶ የተባረረችው ፈረንሳይ ሌላ አፍሪካዊ ሀገር ፍለጋ ላይ መሆኗን ገለጸች

ከማሊ እና ቡርኪና ፋሶ የተባረረችው ፈረንሳይ ሌላ አፍሪካዊ ሀገር ፍለጋ ላይ መሆኗን ገለጸች። ፈረንሳይ ጦሯን ለረጅም ዓመታት ካሰፈረችባቸው ማሊ እና ቡርኪናፋሶ ጋር ያላት ግንኙነት በመበላሸቱ ሀገራቱን ለቃ መውጣቷ ይታወሳል። በቅኝ ግዛት ዘመን ከገዛቻቸው ሀገራት ጋር ያላት ግንኙነት እየተበላሸባት ያለችው ፈረንሳይ ሌሎች ሀገራትን በማማተር ላይ ትገኛለች።

ማሊ እና ቡርኪና ፋሶ የፈረንሳይ ጦር በሀገራችን አለመረጋጋት ሲሰፍን ድጋፍ አላደረገም በሚል ከሀገራቸው አስወጥተዋል። በዚህ ምክንያትም ፈረንሳይ በአፍሪካ ለሚኖራት ማዕከል አጋር ሀገር ፍለጋ ላይ እንደሆነች በፕሬዝዳንት ማክሮን በኩል ገልጻለች።

ፕሬዝዳንቱ ከሚቀጥለው ሳምንት ጀምሮ አራት ሀገራትን ለመጎብኘት ማሰባቸው ሲገለጽ ኮንጎ ብራዛቪል፣ ዲሞክራቲክ ኮንጎ፣ ጋቦን እና አንጎላ የሚጎበኙ ሀገራት ናቸው ተብሏል።ፕሬዝዳንት ማክሮን ወደ አራቱ የምዕራብ አፍሪካ ሀገራት አቅንተው በሁለትዮሽ፣ አካባቢ ጥበቃ እና ሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ከመሪዎች ጋር እንደሚመክሩ ተገልጿል።

በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ከአፍሪካ ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንደሚያጠናክሩ ቃል ገብተው የነበሩት ፕሬዝዳንት ማክሮን ፈረንሳይ ከማሊ፣ ቡርኪናፋሶ፣ አልጀሪያ እና ሌሎች ሀገራት ጋር ያላት ግንኙነት ሻክሯል። እንዲሁም በሩሲያ-ዩክሬን ጦርነት ምክንያት ፈረንሳዊያን ለዋጋ ግሽበት ተጋልጠዋል፣ ፈረንሳይ ለዩክሬን የጦር መሳሪያ ድጋፉን ያቋርጥ እና በሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ የሕዝብ ተቃውሞዎች እየተካሄደባቸው እንደሚገኙ አል ዐይን ዘገባ ያመለክታል።

## ለ20 ዓመታት በጓንታናሞ ቤይ ያለፍርድ ታስረው የቆዩ ወንድማማቾች ተለቀቁ



ሞሐመድ አህመድ ራባኒ

ጓንታናሞ ቤይ ውስጥ በሚገኘው የአሜሪካ ወታደራዊ እርስ ቤት ውስጥ ለሃያ ዓመታት ያህል ታስረው የቆዩ ሁለት ፓኪስታናውያን ወንድማማቾች ምንም ክስ ሳይቀርብባቸው ተለቀቁ። አብዱል እና ሞሐመድ አህመድ ራባኒ ፓኪስታን ውስጥ ተይዘው ከአገራቸው የተወሰዱት በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2002 ነበር።

የአሜሪካ መከላከያ መሥሪያ ቤት አብዱል ራባኒ የተባለው ግለሰብ የአልቃኢዳን የመደበቂያ ቤት ያስተዳድራል እንዲሁም ወንድሙ የቡድኑ መሪዎችን ጉዞ እና ገንዘብን ይመራል ብሎ ነበር። ወንድማማቾቹ ወደ ጓንታናሞ ከመሸጋገራቸው በፊት ከአገራቸው ውጭ በሲአይኤ መኮንኖች ማሰቃየት እንደተፈጸመባቸው ገልጸዋል።

ሁለቱ ፓኪስታናውያን ከአስፈሪው ወታደራዊው እስር ቤት ከተለቀቁ በኋላ ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ተደርጓል። ኩባ ውስጥ የሚገኘው ጓንታናሞ የአሜሪካ ባሕር ኃይል ሰፈር ከመስከረም 11 የሽብር ጥቃት በኋላ ተጠርጣሪዎችን ለማቆያነት የተቋቋመው በቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ጆርጅ ቡሽ አማካይነት ነው።

ካምፑ ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት አሜሪካ ካካሄደችው "ፀረ ሽብር ጦርነት" ጋር በተያያዘ ከተፈጸሙ መጥፎ ድርጊቶች ጋር ስሙ ይነሳል። በተለይ ተጠርጣሪዎች በምርመራ ጊዜ ከባድ ሰቆቃ እንደተፈጸመባቸው እና ያለፍርድ ለረጅም ጊዜ በእስር እንዲቆዩ መደረጋቸው በስፋት ሲነገር ቆይቷል።

ከ20 ዓመት በፊት በጓንታናሞ ውስጥ 680 እስረኞች የነበሩት ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት ግን 32 እስረኞች ብቻ ይገኙበታል። የአሁኑ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ጆ ባይደን እስር ቤቱ እንዲዘጋ እንደሚፈልጉ ተናግረዋል። አሁን ነጻ የተለቀቁት ወንድማማቾች ከ20 ዓመት በፊት በፓኪስታን የደኅንነት ተቋም አማካይነት ካራቺ በተባለችው ከተማ ውስጥ ነበር የተያዙት። ከዚያም አፍጋኒስታን ውስጥ በሚገኝ የሲአይኤ እስር ቤት ለሁለት ዓመታት ቆይተው ነው ወደ ጓንታናሞ ቤይ የተሸጋገሩት።

ከ2013 (እአአ) ጀምሮ ባሉት ሰባት ዓመታት ውስጥ እስሩን በመቃወም አህመድ ራባኒ በተከታታይ የረሃብ አድማ አድርጎ ነበር። የምግብ መድኃኒቶች እየተሰጠው አንዳንድ ጊዜም በኃይል በቱቦ እንዲመገብ እየተደረገ በሕይወት ቆይቷል። የሁለቱ ወንድማማቾች ጠበቃ የሆኑት ክሊቭ ስታፎርድ ስሚዝ ለኒው ዮርክ ታይምስ ጋዜጣ እንደተናገሩት አህመድ ራባኒ በረሃብ አድማው የተነሳ "ከባድ ጉዳት ደርሶበታል" ብለዋል።

ወንድማማቾቹ ከእስር እንዲለቀቁ የተወሰነው ከሁለት ዓመት በፊት ሲሆን፣ ለምን እስካሁን በእስር ላይ እንዲቆዩ እንደተደረገ ግን ግልጽ አልሆነም። አህመድ ራባኒ በቁጥጥር ስር በዋለበት ጊዜ ሚስቱ እርጉዝ የነበረች ሲሆን፣ ከአምስት ወራት በኋላም ወንድ ልጃ ወልዳለች። ላለፉት 20 ዓመታትም አህመድ ከልጁ ጋር ተገናኝቶ አያውቅም።

የሁለቱ ወንድማማቾች እና ሌሎች ከሽብር ጋር በተገናኘ በጓንታናሞ ቤይ በእስር ላይ የቆዩ ሰዎች አያያዝ ሁኔታ እና ጉዳያቸው በፍርድ ቤት አለመታየት በአሜሪካ መንግሥት ላይ ከፍተኛ ተቃውሞን አስከትሎ ቆይቷል። በርካቶቹም ያለፍርድ ለዓመታት በእስር ላይ ከቆዩ በኋላ እንደ ሁለቱ ወንድማማቾች በነጻ መለቀቃቸው ደግሞ በዘፈቀደ የተደረገ እስር ነው በሚል የአሜሪካ መንግሥት የእራሱን ሕግ ጥሷል የሚል ትችትን እንዳስከተለበት ቢቢሲ ዘግቧል።


## የኦዲት ስራ ማስታወቂያ

የቲም ህጻናት እንክብካቤ ማዕከል ሀገር በቀል በጎ አድራጎት ድርጅት በምዝገባ ቁጥር 0195 በፌዴራል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ተመዝግቦ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

በመሆኑም ድርጅቱ የ2022 በጀት ዓመት ሂሳብ በውጪ ኦዲተር ለማስመርመር ስለሚፈልግ በፌደራል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን በተሰጠን መመሪያ መሰረት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት የምትችሉ የኦዲት ድርጅቶች መወዳደር የምትችሉ መሆኑን እየገለጽን ለመወዳደር መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች፡-

ሀ. የታደሰ ንግድ ፈቃድ፤

ለ. የሞያ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት፤

ሐ. የኦዲት ስራ ልምድ፤

መ. የግብር መከፈያ መለያ ቁጥር (Tin Number) ያላቸው አመልካቾች ስራውን ለመስራት ኦዲት የሚያደርጉበትን ዋጋና ስራውን አጠናቀው ማስረከብ የሚችሉበትን ቀን በመጥቀስ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ7 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ከዚህ በታች በተጠቀሰው አድራሻ አስፈላጊውን መረጃ በመያዝ እንድታመለክቱ እናስታውቃለን፡፡

**አድራሻ :- ሰባራ ባቡር በወጋገን ባንክ ፊት ለፊት በሚያስገባው መንገድ 150 ሜትር ገባ ብሎ**

**ስልክ ቁጥር፡ - 0910506992 / 0912204661 / 0912032112**

**ኢ-ሜይል :- yatimccc@yahoo.com**

**የቲም ህፃናት እንክብካቤ ማዕከል**

## የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በፍ/ባለመብት እነ አቶ ቴወድሮስ ሙሉጌታ እና በፍ/ባለዕዳ እነ አቶ ፍፅም ሙሉጌታ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 242757 በ12/11/2013 ዓ.ም እና ሚያዚያ 28 ቀን 2013 ዓ.ም ፤15/3/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በአቃቂ ቃሊት ክ/ከተማ ወረዳ 08 የቤ.ቁ 112/2 ካርታ ቁጥር 015218 የሆነ ይዞታ በአዲሱ የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000070804948 የተቀየረ (የተፈታ ) እና በአቶ ሙሉጌታ ጎባል ተፈራ ስም የተመዘገበ የቤቱ ስፋቱ በሰነድ 842 ካ.ሜትር ሆኖ የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር (2,644,528 (ሁለት ሚሊዮን ስድስት መቶ አርባ አራት ሺ አምስት መቶ ሃያ ስምንት ብር) ሆኖ በአዋሳኞች በምዕራብ ጌታቸው ተስፋዬ ሌላው በአራቱ አቅጣጫ መንገድ የሚያዋስን ሆኖ መጋቢት 28 ቀን 2015 ዓ.ም በሐራጅ ይሸጣል፡ የተጫራቾች ምዝገባ በ4፡00 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡

የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ዴ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ሰዓት ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ለመጐብኘት የሚችሉ ሲሆን፤እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4ኛውን በባንክ በተረጋገጠ C.P.O ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጐድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎችን ዳይሬክቶሬት የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍ/ቤት የፌዴራል ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት**

## የጨረታ ማስታወቂያ

### የጨረታ ቁጥር ኢግ.ሥ.ኮ/ብግጨ/07/2015

የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን በ2015 በጀት ዓመት ለቢሮ አገልግሎት የሚውል ወንበር፣ ጠረጴዛና ሌሎች ተዛማች የቢሮ ዕቃዎችን ከጨረታ ሰነዱ ጋር በተያያዘው ቴክኒካል መስፈርት መሠረት ማቅረብ የሚችሉ ተጫራቾችን በጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ በዘርፉ ፈቃድ ያላችሁና የዘመኑን ግብር ለመክፈላችሁ ማስረጃ የቫት እና ቲን ተመዝጋቢ፤ ከገቢዎች ክሊራንስ ማቅረብ የሚችሉ ተጫራቾች ዘወትር በሥራ ሰዓት ሳሪስ አቦ በሚገኘው ፋፋ የምግብ አ.ማ ጀርባ በሚገኘው የኮርፖሬሽኑ ዋና መ/ቤት ቢሮ ቁጥር 110 ቀርበው የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ የማይመለስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈል የጨረታ ሰነዱን መውሰድ ይችላሉ:: ተጫራቾች ለጨረታው ዋስትና ማስከበሪያ 2% በሲፒኦ ወይም በባንክ ጋራንቲ (Unconditional) ማስያዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የጨረታው ዋጋ ለ60 ቀናት የጸና መሆን ይኖርበታል ::

ጨረታው መጋቢት 12 ቀን 2015 ዓ.ም ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት ተዘግቶ በዚሁ ቀን ከጠዋቱ 4:30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በኮርፖሬሽኑ የስብሰባ አዳራሽ ይከፈታል::

ኮርፖሬሽኑ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው ::


**ለተጨማሪ ማብራሪያ፡- ስልክ 011470-90-95 ወይም 011442-36-08**

**ፋክስ 0114-421312**

**አዲስ አበባ ኢትዮጵያ**

**የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን**

# ስፖርት



## የድሆች አባት- የክርስትያን አትሱ አሳዛኝ መጨረሻ

**አስማየሁ ግዛው**

በስፖርት ታሪክ ውስጥ በርካታ አሳዛኝና ልብ ሰባሪ ክስተቶች ታይተዋል፣ተሰምተዋል። ከአውሮፕላን መከስከስ እስከ ስቴድየሞች የመደርመስ አደጋዎች ተከስተው የበርካታ ስፖርት አፍቃሪያንና የስፖርቱ ተዋናያንን ሕይወት ቀጥፈው ብዙዎችን አሳዝነዋል። የማይረሳ መጥፎ አሻራንም ጥለው አልፈዋል። እኤአ 1989 በእንግሊዙ ማንቸስተር ዩናይትድ የቡድን አባላት ላይ የደረሰው የሙኒክ የአውሮፕላን አደጋ፣ የሊቨርፑል ሂልቦሮ ስቴድየም መደርመስ እንዲሁም በ2016 የብራዚሉ እግር ኳስ ክለብ ቻፓ ክውንሴ ቡድን አባላት ላይ የደረሰውን የአውሮፕላን አደጋ ጨምሮ እጅግ ከባድና ልብ ሰባሪ ክስተቶች ዛሬም ጠባሳቸው አልሻረም፡፡

ከሳምንት በፊት በቱርክና ሶርያ የተከሰተው ከባድ የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ የበርካቶችን ሕይወት ቀጥፏል። ይህም በሬክተር ስኬል 7.8 የተለካ የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ በቱርክና ሶሪያ ድንበር ተከስቶ ከ45ሺ የሚልቁ ሰዎችን ሕይወት በልቷል፡፡ ይህ አሳዛኝ አደጋ ለስፖርት ቤተሰቡም ተርፏል። በአደጋው ሕይወታቸውን ካጡ ሰዎች መካከል በርካታ የስፖርት ሰዎች ይገኙበታል፡፡ በአሳዛኝ ሁኔታ ሕይወቱን በዚሁ አደጋ ያጣው ጋናዊ ኮከብ ተጫዋች ጉዳይ ግን የብዙዎችን አንጀት በልቷል። ለቱርኩ ሀታይስፖር የሚጫወተው ጋናዊው ክርስትያን አትሱ በመሬት መንቀጥቀጥ አደጋው ሕይወቱ ከማለፉ በዘለለ የሞተበት መንገድ የኮከቡን የሕይወት መጨረሻ በትራጄዲ የተሞላ አድርጎታል።

የቀድሞ የእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ ኮከብ በቼልሲና ኒውካስል ሳለ ብዙዎች ያውቁታል። በኳታሩ የዓለም ዋንጫም በጥበበኛ እግሮቹ አገሩን አገልግሏል። በእግር ኳስ ተመልካቾች በሙሉ ይታወቅ የነበረው ጋናዊው አትሱ



ለቱርኩ ሀታይስፖር እየተጫወተ ሳለ በአጋቾች ታግቶ ለበርካታ ሳምንታት እምጥ ይግባ ስምጥ አልታወቀም ነበር። በመጨረሻም ባሳለፍነው ሳምንት በደቡብ ቱርክ ደርሶ በነበረው የመሬት መንቀጥቀጥ ድንገት እስካሁን በሕይወት ያሉ ሰዎች ካሉ በሚል እየተደረገ ባለ አሰሳ ፍርስራሾች ስር እስከወዲያኛው አሸልቦ ተገኝቷል።

አትሱ በበርካታ ፈተናዎች ውስጥ አልፎ ለስኬት በመብቃት ሌሎች እንዲኖሩ እራሱን ሰጥቷል፡፡ ነገር ግን የበርካታ ጋናውያን ህፃናትን ሕይወት የቀየረው፣ በተደጋጋሚ በጠና ለታመሙ የሀገሪቷ ሰዎች ረብጣ ፓውንዶች በማውጣት የህክምና ወጪያቸውን የሸፈነውና፣ በጋና እስር ቤቶች ያሉ ታራሚዎች ጥሩ እንክብካቤን ያገኙ ዘንድ አስመስጋኝ ስራን በመስራት የሚታወቀው ክርስትያን አትሱ በዚህ ሁኔታ ሞቶ መገኘቱ የሁሉም ጋናውያንን ልብ የሰበረ ሆኗል።

አትሱ የተወለደው እ.አ.አ በ1992 በጋና አዳ ፎሃ በሚባል ስፈራ ነው፡፡ የልጅነት ሕይወቱን በጎስቋላ መንደር ውስጥ በፍጹም ድህነት አሳልፎ ለታላቅ ደረጃ በቅቷል። የትምህርት ሕይወቱን ግማሽ ማሳለፍ የቻለው በማዕከላዊ ጎማ ፌተሮ በሚገኘው ፎኖርድ አካዳሚ ነው፡፡ በኋላ ላይ የምዕራብ አፍሪካ እግር ኳስ አካዳሚ የሆነውን ሶጋ ኮፕን መቀላቀል ችሏል፡፡ በመጨረሻም መቀመጫውን ማዕከላዊ ጋና ወዳረገው ቼታሃ እግር ኳስ ክለብ አቅንቷል፡፡

አትሱ የአፍሪካ ቆይታውን አገባዶ ወደ አውሮፓ በማቅናት በ17 ዓመቱ የፖርቹጋሉን ክለብ ፖርቶን መዳረሻው ማድረግ ችሏል፡፡ በግንቦት 2011 በወቅቱ የፖርቶ አሰልጣኝ በነበረው አንድሬስ ቪላስ ቦዋስ ለፖርቶ መጀመሪያ ቡድን እንዲጫወት ቢመረጥም በወቅቱ መጫወት አልቻለም ነበር፡፡ አትሱ በ2011-12 የውድድር ዘመን በዚያው ሊግ ለሚወዳደረው ሪዮ አቬ በውሰት ተሰጥቶ ተጫውቷል። የመጀመሪያ ጨዋታውንም በነሐሴ 2011 ቡድኑ 1-0 በተሸነፈበት ጨዋታ ተሰልፎ መጫወት ችሏል፡፡ አትሱ በታኅሳስ 2011 ቡድኑ በስታዲዮ ዳሉዝ ከቤኔፊካ ጋር ባካሄደው ጨዋታ በ24ኛው ደቂቃ ለክለቡ የመጀመሪያውን ጎል ማስቆጠር ችሏል፡፡ በ2013 ወደ እናት ክለቡ ፖርቶ ተመልሶ ለሶስት ተከታታይ ጊዜ ዋንጫ ሲያነሳ በዘጠኝ ጨዋታዎች መሰለፍ ችሏል፡፡ በወረሃ መስከረም 2013 አትሱ ፖርቶን ለቆ በ3.5 ሚሊየን ዩሮ የእንግሊዙ ክለብ ቼልሲ ንብረት ሆነ፡፡ ብዙም ሳይቆይ ለሆላንዱ ክለብ ቪቲዜ በውሰት ተሰጠ፡፡ የሆላንድ ቆይታውን አጠናቆም ሲመለስ በ2014 ለመርሲ ሳይዱ ክለብ ኤቨርተን በውሰት ተጫውቷል፡፡ ሌሎች በውሰት የተጫወተባቸው ክለቦች በርንማውዝና የስፔኑ ማለጋ ተጠቃሽ ናቸው።

አትሱ ሌላው መጫወት የቻለበት ክለብ ኒውካስትል ዩናይትድ ነው፡፡ በኒውካስትል የ2016-17 የውድድር ዘመንን በውሰት ከቆየ በኋላ በግንቦት 2017 በዛው ለመቆየት የቋሚነት ፊርማውን አኑሯል፡፡ በኒውካስትል በቆየባቸው አራት አመታት ጥሩ የሚባል እንቅስቃሴን በማድረግ ኮንትራቱ በመጠናቀቁ ወደ ሳውዲ በማቅናት ለአልራድ መጫወት ችሏል፡፡ በዛ የአንድ አመት ቆይታን ካደረገ በኋላ ወደ ቱርኩ ሀታይስፖርት በማቅናት ሕይወቱ እስካለፈችበት ቀን ድረስ በሀታይስፖር ንብረት ነበረ።

የ31 ዓመቱ ኮኮብ በአሳዛኝ ሁኔታ መሞቱን በወኪሉ ናና ሲቸር አማካኝነት በትዊተር ነበር የተገለፀው። በወቅቱም ወኪሉ እንዲህ በማለትም መልእክቱን በተሰበረ ልብ አስተላልፏል። " ይሄን ነገር ሳረጋግጥ በከባድ የልብ ስብራት ውስጥ ሆኜ ነው፣ በጎ ነገርን ለተመኙልን ሁሉ በሚያሳዝን መልኩ የክርስትን አትሱ አካል በዚህ ማለዳ ለማሳወቅ እወዳለሁ፣ እናም ከልብ የመነጨ መጽናናኛዬን ለቤተሰቡና ለሚወዱት በሙሉ እንዲሆንልኝ፡፡ ይሄን እድል ተጠቅሜ በጸሎትና ሌሎች እገዛዎች ከጎናችን ለነበሩት በሙሉ ላመሰግን እወዳለሁ" በማለት ተናገሯል፡፡

አትሱ ለብሔራዊ ቡድኑ ለመጀመሪያ ጊዜ ተሰልፎ መጫወት የቻለው በ2012 ከሌሴቶ ጋር ነው። በወቅቱም ጎል ያስቆጠረ ሲሆን በቢቢሲ ጥሩ ተጨዋች እንደሆነ ተሞካሽቶ ነበር።

አትሱ ለጋና ብሔራዊ ቡድን በ2015 የአፍሪካ ዋንጫ ባደረገው ተሳትፎ ባሳየው ብቃት የውድድሩ ምርጥ ተጨዋች ለመባል ችሏል። የውድድሩንም ምርጥ ግብ ያስቆጠረ ተጨዋች ነበር። በ2018 እና በኳታሩ የዓለም ዋንጫም ሀገሩን በመወከል ምርጥ ብቃቱን ማስመልከት ችሏል።

የቀድሞ ክለቡ ቸልሲ ለመላው ቤተሰቡና ጓደኞቹ መጽናናትን ተመኝቷል። አትሱ በበጎ አድራጎት ስራዎች በነቂስ የሚሳተፍ ሲሆን በዛም አምባሳደር በመሆን የተቸገሩ ሰዎችን በመርዳት ይታወቃል።




## የአፍሪካ ኩራት ዓድዋ

**በስጥሳቸው ልውልሰገድ**

ሰላም ልጆች እንዴት ናችሁ:: ሳምንቱ እንዴት አለፈ? ትምህርት እንዴት ነበር? እንደተለመደው ሳምንቱን በትምህርት እና በጥናት እንዳሳለፉችሁ እርግጠኛ ነኝ:: ምክንያቱም እናንተ ጊዜያችሁን በአግባቡ የምትጠቀሙና በትምህርታችሁ የማትደራደሩ መሆናችሁን ስለማምን ነው::

ሀገራችን በምን ውስጥ አልፋ ለዛሬ እንደደረሰች መረዳት ባህሏን ማወቅ ማክበርና ለሌሎች ማስተዋወቅ ሀገሩን ከሚወድ ልጅ የሚጠበቅ ትልቅ ቁም ነገር ነው:: በዛሬው ፅሁፌ ኢትዮጵያን በዓለም ዙሪያ ጎልታ እንድትታይና እንድትከበር ያደረጋትን እንዲሁም የአፍሪካም ኩራት የሆነውን የዓድዋ ድልን እንመለከታለን::

በ1882 ዓ.ም ጥቅምት ወር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው የነገሡት ዳግማዊ አፄ ምኒልክ በዓድዋ ጦርነት የኢትዮጵያን ስም በዓለም አስጠሩ። ምኒልክ ንግሥናቸውን እንዳገኙ የመጀመሪያው የውጭ ጉዳይ ውል ከኢጣልያ ጋር የተደረገው ነበር። ይህም የስምምነት ውል የውጫሌው ውል በመባል የሚታወቀውና ለዓድዋ ጦርነት መነሻ የሆኑ አንቀጾችን የያዘው ስምምነት ነው። የውጫሌ ውል አንቀጽ አሥራ ሰባት የጣሊያንኛው እና የአማርኛው የተለያየ ትርጉም ነበረው፤ የጣሊያንኛው "ኢትዮጵያ ከአውሮፓ መንግሥታት ጋር ማድረግ የምትፈልገውን ግንኙነት በኢጣሊያ መንግስት በኩል ማድረግ አለባት" ሲል፤ የአማርኛው ደግሞ "ኢትዮጵያ ከአውሮፓ መንግሥታት ጋር ማድረግ የምትፈልገውን ግንኙነት በኢጣሊያ መንግሥት በኩል ማድረግ ትችላለች "ይላል::

ልጆች ይህ የውጫሌ ስምምነት የአማርኛው ትርጉም የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና ልዕልና ሲያስከብር በተቃራኒው የጣሊያንኛው ትርጓሜ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና ልዕልና መድፈር ብቻ ሳይሆን ብሔራዊ ክብሯንና ጥቅሟን ይነካል:: ዳግማዊ ምኒልክ አርቆ በማሰብ ኢትዮጵያ በኢጣሊያ



መንግሥት ቁጥጥር ስር እንዳትገባ ጥረት በማድረግ ነፃነታቸውን ጠብቀው ከሌሎች ሀገራት ጋር ግንኙነትንና ምክር መቀበል ቀጠሉ። በዚህም የተነሳ ኢጣሊያንም ኢትዮጵያን ለመያዝ በኤርትራ በኩል ትግራይን መውረር ጀመረች። ምኒልክም ሕዝቡን ለጦርነት ክተት አሉ።

ልጆች አፄ ምኒልክ በወቅቱ ያስነገሩት አዋጅ ምን የሚል መሰላችሁ፤ "እግዚአብሔር በቸርነቱ እስካሁን ጠላት አጥፍቶ አገር አስፍቶ አኖረኝ፤ እኔም እስካሁን በእግዚአብሔር ቸርነት ገዛሁ:: ከእንግዲህ ብሞትም ሞት የሁሉም ነውና ስለእኔ ሞት አላዝንም:: ደግሞ እግዚአብሔር አሳፍሮኝ አያውቅም፤ ወደፊትም ያሳፍረኛል ብዬ አልጠራጠርም:: አሁንም አገር የሚያጠፋ፤ ሃይማኖትን የሚለውጥ፣ በፊት እግዚአብሔር የወሰነልንን ባህር አልፎ መጥቷል:: እኔም የአገሬን ከብት ማለቅ፤ የሰውን መድከም አይቼ እስካሁን ዝም ብለው ደግሞ እያለፈ እንደፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር:: አሁን ግን በእግዚአብሔር ረዳትነት አገሬን አሳልፌ አልሰጠውም:: የአገሬ ሰው ከአሁን ቀደም የበደልሁህ አይመስለኝም:: አንተም እስካሁን አላስቀየምኸኝም:: ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ። ጉልበት የሌለህ ለልጅህ፣ ለምሽትህ፣ ለሃይማኖትህ ስትል በሃዘንህ እርዳኝ:: ወስልተህ የቀረህ ግን ኋላ ትጣላኛለህ:: አልምርህም:: ማርያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም። ዘመቻዬ በጥቅምት ነውና የሸዋ ሰው እስከ ጥቅምት እኩሌታ ወረይሉ ከተህ ላግኝህ።" የሚል አዋጅ ነበር:: በዚህ አዋጅ መሰረት ጀግናና ቆራጥ የነበሩት የጥንት አባቶቻችን ሁሉን ነገር ጥለው ቅድሚያ ሀገሬን ብለው ለዘመቻ ወጡ::

ጣሊያኖች በጄኔራል ባራቲዬሪ የሚመራውን 20 ሺህ ወታደሮቻቸውን ይዘው በ1888 ዓ.ም የካቲት 23 ቀን ዓድዋን ወጉ። ከ 80 ሺህ እስከ 120 ሺህ የሚገመተው የኢትዮጵያ ሠራዊትም በሚገባ ሲዋጋ የሀገሪቱ ተፈጥሯዊ አቀማመጥና ሀገሬን ብሎ በቁርጠኝነት ስሜት ቀፎው እንደተነካ ንብ የተነቃነቀው ኃይል የጠላትን ጦር አደናግጦ መግቢያ መውጫ በማሳጣት ቀኑን ሙሉ ጦርነቱ ከተካሄደ በኋላ በሚያስደንቅ አኳኋን ድሉ የኢትዮጵያ ሆነ። ልክ የዛሬ 127 ዓመት። ሃያ ዘጠኝ ሺህ ፈረሰኞችን ጨምሮ ከመቶ ሺህ እስከ መቶ ሃያ ሺህ የሚገመት አንድ ሺህ ኪሎ ሜትር በባዶ እግሩ የተጓዘ የኢትዮጵያ የገበሬ ሠራዊት በወታደራዊ አካዳሚ የሠለጠነውን የአውሮፓ ወራሪ ጦር የካቲት 23 ማለዳ አሥራ አንድ ሰዓት ግድም ገጥሞ ከረፋዱ አራት ሰዓት ላይ ማሸነፉን አረጋግጧል:: ቅኝ አገዛዝ እግሬ አውጪኝ ሲል ነፃነት በኢትዮጵያ ምድር ላይ ከፍ አለ። ለጥቁር ሕዝብ የነጻነት ተጋድሎ ጮራው ፈነጠቀ። ኢትዮጵያ በልጆቹዋ ደምና አጥንት ሉዓላዊነቷን አረጋገጠች። በቅኝ ግዛት ለተያዙ ሌሎች የአፍሪካ ሀገራትም ምሳሌ ሆና የተስፋ ብርሃንን አበራችላቸው::

ልጆች እቴጌ ጣይቱ በጡል ለዓድዋ ጦርነት መንስኤ የሆነውን የውጫሌ ውል አንቀጽ 17 ኢጣሊያኖች ትርጉሙን አዛብተው ኢትዮጵያን በመዳፋቸው ስር ለማስገባት የሸረቡትን ሴራ ቀድመው ማጋለጣቸው ይነገርላቸዋል፤ በተለያዩ የታሪክ መፃህፍት ላይ ሰፍሮ እናገኘዋለን:: እቴጌ ጣይቱ ከባለቤታቸው ከአፄ ምኒልክ፣ ከኢትዮጵያውያኑ የጦር አዝማቾችና ሠራዊታቸው ጋር በመሆን ከተፋፋመው የዓድዋው ጦር ግንባር ላይ በመገኘት ጦሩን ከማበረታታት በላይ የመቀሌን ምሽግ በውኃ የሰበሩ ጀግና ናቸው። የመቀሌው የጣሊያን ጦር ምሽግ ጠንካራነት ጣይቱን ለፈጣን መላ ጋበዘ። ለአጃቢ ወታደሮቻቸው የመስዋዕትነት ግብዣ አቀረቡ። እነዚያ ወታደሮች የመቀሌውን የጣሊያን ጦር የመጠጥ ምንጭ ያዙ። ጣሊያን የሆዱ ነገር አሸነፈውና የመቀሌው ምሽጉ ባስደናቂ ሁኔታ ተሰበረ። የጣይቱ ብልህነት ወራሪውን ጣሊያን ድል መታ::

እንግዲህ ልጆች ኢትዮጵያ ታላቅ ክብርና ያገኘችበትና ነፃነቷን አላስነካም ያለችበትና በየአመቱ የካቲት 23 ቀን የሚከበረው የዓድዋ ድል ታሪክ ይህንን ይመስላል:: ጦርነት ጥሩ ባይሆንም አባቶቻችን ሀገራችንን ከጠላት ለመጠበቅ የሕይወት መሰዋዕትነት ከፍለው ለዚህ አድርሰዋል:: እናንተ ደግሞ ጠንክራችሁ በመማር ሀገራችሁን ከኋለ መቅረት ጦርነት ነፃ ልታወጧት ይገባል እያልኩ በዚሁ አበቃሁ መልካም ሳምንት::